# አዲስ ዘመን

እኢንድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 015 መስከረም 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# አሸባሪው ትሕነግ በአማራና አፋር ክልሎች የፈፀማቸው ወንጀሎች በአመራሩ ታቅደው መፈጸማቸው ተረጋገጠ



ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትሕነግ ሒሳብ አወራርዳለሁ በሚል የፈፀማቸው የጅምላ ግድያ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ዘረፋ እና የማሰቃየት ወንጀሎች በመጀመሪያ ምዕራፍ ምርመራ መረጋገጣቸውን የሚኒስትሮች ግብረኃይል ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። ሁሉም ዓይነት ድርጊቶች በድንገት የተደረጉና በታጣቂዎች ፍላጎት ላይ ተመስርተው የተፈፀሙ ሳይሆኑ በአሸባሪው ትሕነግ አመራሮች ታቅደውና ታስቦባቸው ለመደረጋቸው ማረጋገጫ የሚሆኑ ሰነዶች፣ የሰው ምስክሮችና የተለያዩ ማስረጃዎች በምርመራ ሊገኙ መቻላቸውን አቶ ፈቃዱ ተናግረዋል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታና የግብረኃይሉ አባል አቶ ፍቃዱ ጸጋ እንደገለፁት፤ አሸባሪው ትሕነግ በአማራና በአፋር ክልሎች በፕሮፖጋንዳ ደረጃ ሒሳብ አወራርዳለሁ በሚል ሲነዛ የቆየውን ትርክት ተግባራዊ ማድረጉ በምርመራ ተረጋግጧል።

አሸባሪው ትሕነግ በአማራና አፋር ክልል ያደረሳቸው ጥፋቶችን በተመለከተ ከሚኒስትሮች ግብረኃይል መቋቋሙ በፊት ምርመራ ተጀምሮ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ፈቃዱ፤ በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ከተፈፀመበት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በክልሎቹ በጦርነቱ

አሸባሪው ትሕነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

# የሸኔ አባላት ከአሸባሪው ትሕነግ ታጣቂዎች ጋር ተሰልፈው በግንባር ሲዋጉ ተይዘዋል

ጌትነት ተስፋማርያም

ሁለቱ አሸባሪዎች ትሕነግ እና ሸኔ ኢትዮጵያን ለማፍረስ አብረው ለመሥራት እንደተስማሙና እየሠሩ መሆናቸውን መግለጻቸው ይታወቃል።

አሸባሪው ትሕነግ በሁለት ዙር በከፈተው ጦርነትና በፈጸመው ወረራ በአማራ እና አፋር ክልሎች ላይ ከፍተኛ ውድመት አድርሷል፤ ንጹሀንን ገድሏል፤ ከአርሶ አደሩ ጓዳ

የሸኔ አባላት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢትዮ- ጅቡቲ የምድር ባቡር ለኢኮኖሚ ሽግግሩ ወሳኝ አቅም እየሆነ ነው

## - በ2014 ከአጠቃላይ የወጪ ገቢ ጭነት 11 በመቶ በባቡር ተሸፍኗል

ወርቁ ማሩ



ፎቶ፡- ሳሙኤል ተስፋዬ

ድሬዳዋ፡- የኢትዮ- ጅቡቲ የምድር ባቡር ለሁለቱ አገራት ልማት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እያደገ መምጣቱን የኢፌዴሪ የገንዘብ ሚኒስትርና የማህበሩ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ አህመድ ሺዴ ተናገሩ። በ2014 በጀት ዓመት ከአጠቃላይ የወጪ ገቢ ጭነት ውስጥ 11 በመቶ በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የተሸፈነ መሆኑ ተጠቁሟል።

የኢትዮ-ጅቡቲ አክሲዮን ማህበር 13ኛ መደበኛ የቦርድ አመራር አባላት ጉባኤ ትናንት በድሬዳዋ ከተማ ሲካሄድ የቦርዱ ሰብሳቢ አቶ አህመድ ሺዴ እንደተናገሩት፤ ማህበሩ ለሁለቱ አገራት የጋራ ኢኮኖሚያዊ እድገት እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦ እያደገ መጥቷል።

ሁለቱን አገራት በልማት በማስተሳሰርና ተያይዞ ለማደግ የባቡር መሠረተ ልማቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ያሉት አቶ አህመድ፤ በቀጣይም አገልግሎቱን ለማሳደግ መንግሥት ቁርጠኛ ሆኖ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ አህመድ እንዳሉት፤ በሁለቱ አገራት መካከል የሚካሄደውን ዘርፈ-ብዙ የልማት ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው።

ዘርፉ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ በተለይ ከጸጥታ አንጻር ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አህመድ፤ በቀጣይም ማህበሩ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በማሳደግ የሁለቱን አገራት ኢኮኖሚ ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በትኩረት ይሠራል ብለዋል። በቦርድ ስብሰባው ላይም የሁለቱ አገራት የፖሊስ አመራሮች እንዲሳተፉ መደረጉን ጠቁመዋል።

በዚህም መሠረት ቦርዱ ያሉበትን ችግሮች ለመፍታት መንግሥት ቁርጠኛ ሆኖ መሥራቱን አቶ አህመድ ጠቁመው፤ ይህ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል።

የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር አብዲ ዘነበ በበኩላቸው፤ መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ተቋሙ የነበሩበትን በርካታ ችግሮች እየፈታ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮ- ጅቡቲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# የኢሬቻ በዓል የቀደመውን ባህላዊና ትውፊታዊ ሥርዓት ጠብቆ እንዲከበር ጥሪ ቀረበ

ገጽ 4






## ከአንጋፋ ጋዜጠኞች ጀርባ ያሉት

- ጠንካራው ጠንክር



ገጽ 6

# ኢንስቲትዩቱ ወቅታዊ የአየር ትንበያ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዳማ፡- ጥራት ያላቸውና ወቅታዊ የአየር ትንበያ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ተቋማትና ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የጀመራቸውን የለውጥ ሥራዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ የክረምት ወቅት ትንበያ ግምገማና የመጪው የበጋ ወቅት የአየር ጸባይ ትንበያ ላይ ሰሞኑን በአዳማ ከተማ ውይይት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ ጥራት ያላቸውና ወቅታዊ የአየር ትንበያ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ተቋማትና ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የጀመራቸውን የለውጥ ሥራዎች አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

የአየር ትንበያ መረጃ ሥራዎቹ በጊዜ፤ በመጠን፣ በቦታና በጥራት በማዘጋጀት ተደራሽ የማድረግ ሥራ ኢንስቲትዩቱ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ቁርኝት ባላቸው የተፈጥሮ አደጋዎች ላይ ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ ያስችላል ብለዋል፡፡

በደንበኞች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎቶችን በወቅቱና በጥራት ለማሰራጨት ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተን እንሠራለንም ብለዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የአየር ጸባይ ክስተቶች ሊያሳድሩ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን በመከታተል መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ ቅድመ ጥንቃቄ ይረዳ ዘንድም ለተጠቃሚዎች የማድረስ ሥራ እየተከናወነ ነው፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢታፋ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የመጪው በጋ ወቅት ዝናብ ከሚጠበቀው በታች ስለሚሆን ሊከሰት የሚችለውን የድርቅ አደጋ ለመቀነስ ዝግጅት እየተደረገ ነው ።

በደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅና ምሥራቅ ኢትዮጵያ የበጋ ዝናብ ከመደበኛ በታች ሊሆን ስለሚችል የኅዳር፣ ታኅሣሥና ጥር ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የዝናብ እጥረት የሚፈጠርበት ዕድል ሰፊ ነው ብለዋል።

ሚኒስትሩ በቆላማው የአገሪቷ አካባቢዎች የከርሰ ምድር ውሃን ለልማት ለማዋል በትኩረት እንደተሠራ ገልጸው፤ የአየር ሁኔታ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን ወስደን ተግባራዊ በማድረጋችን ድርቁ ሊያስከትል የነበረውን የከፋ ጉዳት መቋቋም ተችሏል ብለዋል።

ባለፈው የተከሰተው ድርቅ በእንስሳት ሀብቱ ላይ ጉዳት ቢደርስም የሰው ሕይወት ላይ አደጋ እንዳያደርስ ማድረግ ችለናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የጎርፍ አደጋ እንዳይከሰት የአየር ሁኔታ ትንበያ መረጃዎችን በመከታተል የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎች በመሠራታቸው በተለይ በከተሞች የውሃ መውረጃ ቦዮች ፅዳትና በግብርና ዘርፍ ተገቢው ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል።



# የሀዲያ የዘመን መለወጫ «ያሆዴ በዓል» ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል

**መሳኩ ኤሮሴ**

ከሆሳዕና፡- የሀዲያ ብሔር ዘመን መለወጫ የሆነው ያሆዴ በዓል ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ የሚመለከታቸው አካላት በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ አመለከቱ።

አቶ ቀጄላ መርዳሳ የያሆዴ በዓል ትናንት በሆሳዕና ከተማ ሲከበር እንደገለጹት፤ ያሆዴ የሀዲያ የዘመን መለወጫ ነው። በዓሉ የሀዲያ ሕዝብ የሚገለጽበት ታሪካዊ ቅርስ እና ጥንታዊ ስልጣኔ ነው። ይህ በዓል ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ የሚመለከታቸው አካላት በትኩረት ሊሠሩ ይገባል።

በዓሉ ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ ሳይበረዝ ለቀጣይ ትውልድ መተላለፍ እንዳለበት ያመለከቱት አቶ ቀጄላ፤በዓሉ ባህላዊ ትውፊቱን ጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የበኩሉን እንደሚወጣ አረጋግጠዋል።

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ፋጤ ሰርሞሎ በበኩላቸው ያሆዴ የዘመን መለወጫ ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ የሚገቡ እሴቶችን አቅፎ የያዘ ትልቅ በዓል ነው ብለዋል።

ከእነዚህ መካከል የአብሮነት፣ የአንድነት፣ የመቻቻል፣ የፍቅር፣ የመረዳዳት እና የመልካምነት እሴቶች የሚታይበት በዓል መሆኑን ጠቁመው፤ እነዚህን መልካም እሴቶች በበዓሉ ወቅት ለብሔሩ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የሚያካፍሉበት ቀን ሲሆን በተለይም የእርቅ ሥነ ሥርዓቱ ከያሆዴ በዓል ጋር ቁርኝት አለው። በያሆዴ ሰሞን የተጣሉት እንደሚታረቁ ገልጸዋል። የሀዲያ አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች የተለያዩ ጫናዎችን ተቋቁመው በዓሉን ለዚህ እንዲበቃ በማድረጋቸው ክብር ይገባቸዋል ብለዋል።

የዞኑ አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም መጫ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ያሆዴን ከሌሎች በዓላት ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል የተራራቀ የሚቀራረብበት፣ አቅም ያለው ለሌለው የሚያካፍልበት፣ የተጣላው የሚታረቅበት ሁሉም ጠግቦ የሚበላበትና የሚቦርቅበት መሆኑ ነው። ለዚህም ነው «አንቺ ዮ ፎር ያሆጥ በላ ጎዶኮ» የሚባለው ትርጓሜውም ከባለቤቱ ጋር የሰነበተች ነፍስ የያሆዴ ዕለት ትጠግባለች ማለት ነው። በያሆዴ ቀን የሚራብ አይኖርም። እንስሳት እንኳ የያሆዴ ቀን አይራቡም ሲሉ አብራርተዋል።

ያሆዴ ሁሉም የቤተሰብ አባላት የየድርሻቸውን የሚወጡበት ነው ያሉት አቶ አብርሃም፤ ያሆዴ የአዲስ ዓመት እቅድ የሚዘጋጅበትና መልካም ምኞት የሚገለጽበት መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አብርሃም ገለጻ፤ አብዛኛው ጊዜ አባቶች ልጆችን የሚመርቁ ሲሆን የያሆዴ ቀን ግን ልጆች ወላጆችን የሚመርቁበት መሆኑ ቀኑን ለየት ያደርገዋል። ያሆዴን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# የአምራች ኢንዱስትሪውን በዘላቂነት ለማሳደግ ተተኪው ትውልድ ላይ መስራት ያስፈልጋል

**አዲሱ ገረመው**

ቢሾፍቱ፡- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንድትሆንና የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ በዘላቂነት ለማሳደግ ተተኪው ትውልድ ላይ መሥራት እንደሚገባ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል አመለከቱ። የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሠራተኞችና አመራሮች ልጆች ወላጆቻቸው ለአገር ምን እየሠሩ እንደሆነ ጉብኝት አካሂደዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሠራተኞችና አመራሮች ልጆች ወላጆቻቸው ለአገር ምን እየሠሩ እንደሆነ በማስጎብኘት የሥራ አጋር እንዲሆኑና አምራች ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ በማሰብ የመስክ ምልከታ መርሀ ግብር ትናንት በአዳማና ቢሾፍቱ አካሂደዋል።



ፎቶ፡- በገበቡ ገብሬ

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ለጎብኚዎቹ ሽኝት ባደርጉበት ወቅት፣ ጉብኝቱ ልጆች ወላጆቻቸው በኢንዱስትሪው ዘርፍ ምን እያከናወኑ እንደሆነ ግንዛቤ የሚሰጥ እንዲሁም የኢትዮጵያን ምርታማነትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድረግ ተተኪው ትወልድ ትልቅ ሚና እንዳለው ለማስገንዘብ እንደተዘጋጀ ገልጸዋል።

በዓለም ላይ ትላልቅ የሚባሉ አገራት የበለጸጉት ኢንዱስትሪን በማስፋፋታቸው ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ዜጎች ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ተግባራት ማወቅ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

የአገርን ገቢ ለማሳደግና በኢኮኖሚ ለመብለጽግ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሚናው ከፍተኛ እንደሆነ በመግለጽ፣ ዜጎች ከልጅነት ዕድሜያቸው ጀምረው በምርምርና ጥናት ታግዘው የአገራቸውን የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ተሞክሮ መቅሰም እንዳለባቸው አመልክተዋል።

ኢትዮጵያን ጠንካራ አገር ለማድረግ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ ተተኪው ትውልድ ላይ መሥራት ይገባልም ነው ያሉት ሚኒስትሩ። በዚህም ታዳጊዎች መስኩ ለአገር እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ተመልክተው ወደፊት በዚህ ዘርፍ ሲሰማሩ የአገር አለኝታነታቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በጉብኝቱ ወቅት የአገራቸውን የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ መመልከታቸው ለወደፊቱ አገርን ተረክበው ዘርፉን ለማሳደግ መነሳሳትን እንደፈጠረባቸውም ጎብኚ ሕፃናቱ ተናግረዋል። የመስክ ምልከታው በአዳማና ቢሾፍቱ አካባቢ የሚገኙ የብስኩት፣ ኢንዶሚንና መሰል አምራች ኢንዱስትሪዎችን ያካተተ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኮሚሽኑ «ሪፖርት»በአፍሪካውያን ውድቅ መደረጉ አፍሪካውያን ሁሌም ከእውነት ጋር የመቆማቸው አንዱ ማሳያ ነው !

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ቡድን ሰሞኑን ያወጣው ‹‹ሪፖርት›› የፖለቲካ ተልዕኮ ያለው፣ ሳይንሳዊ የጥናት መንገድን ያልተከተለ፣ ወደ አንድ ጎን ያደላ፣ በሀሰተኛ መረጃ የታጨቀ መሆኑን በመግለጽ ኢትዮጵያ እንደማትቀበለው አስታውቃለች።

‹‹ሪፖርቱ›› ገና ከመነሻውም የታቀደው ለሰብዓዊ መብት ከመቆርቆርና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዲታረሙ ከመፈለግ ሳይሆን የፖለቲካ ፍላጎትንና ዓላማን አንግቦ መሆኑን በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ እና ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። በግልጽ ለማየት እንደተቻለውም ዓላማው ፖለቲካዊ ፍላጎትን ለማስፈጸም ነው። የ“ሪፖርቱ” ዋነኛ ዓላማ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና ማሳደር፤ በአፍሪካ ክብርና ዝና ያለውን የኢትዮጵያን የአገር መከላከያ ሰራዊት ስምና ዝና ማጠልሸት ነው።

ዓይን ያወጣ አድሎም የታየበት ነው። “ሪፖርቱ” በሚፈለገው መልኩ ተቀናብሮና ተቀንብቦ መውጣት ብቻም ሳይሆን እንዲወጣ የተደረገበት ጊዜም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው። በዚህ ወቅት እንዲወጣ የተፈለገውም አንዱ ምክንያት የተመድ ስብሰባን አስታኮ በሀሰተኛ ሪፖርት አገሪቱን ለመኮርኮም ጭምር ነው። ይሁን እንጂ ‹‹እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል›› እንዲሉ የሸፍጠኞቹ ሸፍጥ በሲውዘርላንድ በጄኔቫ በተካሄደው በ51ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ ተጋልጧል።

አንዳንድ የሴራው ተባባሪና የአሸባሪው ትህነግ ደጋፊዎችና የኢትዮጵያ ጥንካሬና ዕድገት ጠል ኃይሎች ሲቀሩ ሌሎች ሀቀኞች ግን ሪፖርቱን ፖለቲካዊ አጀንዳን ያነገበ ሲሉ አጣጥለውታል። ሰብዓዊነትን ሳይሆን ፖለቲካዊ ተልዕኮ የተጫነው መሆኑንም በአደባባይ መስክረዋል።

አሸባሪው ትህነግ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በአገር መከላከያ ሰራዊት ላይ የክህደት ጥቃት ከመፈጸም ጀምሮ በአፋርና በአማራ ክልሎች ላይ በተለያየ ቦታ በአሰቃቂ ሁኔታ ዜጎችን በማንነታቸው ጨፍጭፏል፤ በማይካድራ፣ ጭና ጋሊኮማ እና በሌሎች ቦታዎች በንጹሀን ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋና በየቦታው የተገኘው የጅምላ መቃብር ምስክር ነው። መነኩሴና ህጻናት ሴቶች ሳይቀሩ ደፍረዋል። በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎችን አፈናቅሏል፤ የመንግስትና የግለሰቦችን ንብረት አውድሟል፤ አቃጥሏል። ዘግናኝና አሳፋሪ የሆኑ የሰብዓዊ መብት በደሎችን በአደባባይ ፈጽሟል። ይሁን እንጂ ይህንን ሀቅ አፍረጥርጦ ለማውጣት ሪፖርቱ አቅም አንሶት ታይቷል። የሽብር ቡድኑን ኢሰብዓዊ ተግባር ከማጋለጥ ይልቅ ለመሸፋፈን ሞክሯል።

እየተወገዘ ያለው የሰላም በሮችን ከፍቶ ለሰላም እጁን የዘረጋው መንግስት መሆኑ ደግሞ ያስደምማል። በመሆኑም አንዳንድ የዓለም መንግስታት በጭፍን አሸባሪውን ትህነግን እየደገፉ መሆኑ በቀጥታም ሆነ በስውር ከሚያደርጓቸው ድርጊቶች ከሚያወጣቸው ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል። እነዚህ መንግስታት የኢትዮጵያን ሁኔታ በትክክል አይረዱም ማለት አይቻልም። በተለያየ መልኩ ማን ምን አደረገ፣ የት ምን አደረገ የሚለውን መረጃ የሚያገኙበት መንገድ አለ። ሆኖም ግን የሚያውቁትን መረጃ እንደማያውቁ፣ እንዳልሰሙና እንዳላዩ በመሆን በመንግስት ላይ ጫና ማድረግን መርጠዋል። ይሄ ተገቢና ትክክል አይደለም። ከታሪክ ተወቃሽነት አያድንም።

አሸባሪው ትህነግ በንጹሃን ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸሙን በመረጃና በማስረጃ ተረጋግጦ እየቀረበና እየታየ እንኳን አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ድርጊቱን አይቶ እንዳላየ ሲያልፉት በተደጋጋሚ ተስተውሏል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ጥገኛ የሆነች፤ ሁልጊዜ የእርዳታ እህል እየለመነች የምትኖር አገር መፈለጋቸው ነው፡፡

ኢትዮጵያ የውስጥ ችግሯን በራሷ የመፍታት አቅም አላት። አሁን እየተካሄደ ያለውም ህግ ማስከበር፤ የአገርን ሰላም እና ሉዑላዊነት ማረጋገጥ የአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ አገራት በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ እጃቸውን ሊያጠልቁ ሲሞክሩና ፍትህን ሲያዛቡ ይስተዋላል። አሁንም ይሄንኑ ጣልቃ ገብነት በተዘዋዋሪ መንገድ እያሳዩ ነው።

ኢትዮጵያ ሁልጊዜም የአንድ አገር የውስጥ ጉዳይ በአገሩ ህግ መሰረት መፈታት አለበት የሚል አቋም አላት። ከዛ ከፍ ካለ ደግሞ የአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄን ታራምዳለች። ችግሮች ሁሉ በዚሁ መልኩ እንደሚፈቱና የሌሎች ጣልቃ ገብነት እንደማያስፈልግም አጥብቃ ታምናለች።

የተባበሩት መንግስታት ያወጣውን ሪፖርትም አፍሪካውያን የማይቀበሉት መሆናቸውን ሲያሳውቁም በአፍሪካ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ችግር አገራት በራሳቸው መፍታት ይችላሉ ከሚል አቋማቸው የመነጨ ነው። ችግሮቻችንን በራሳችን የመፍታት አቅምም ሆነ ዝግጁነት አለን ሲሉም ከኢትዮጵያ ጎን ቆመው በአደባባይ አቋማቸውን አንጸባርቀዋል። ይህም አፍሪካውያን ለአፍሪካ መፍትሄ መሆናቸውንና ሁሌም ከእውነት ጋር የመቆማቸው ማሳያ ነው!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ለአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ውጤታማነት...

አዲሱ ባይከዳኝ

ትምህርት የሁሉ ነገር መሰረት ነው ሲባል ለአገር እድገት ከሚጫወተው ሚና እና ለሰው ልጅ አስተሳሰብ አድማስ መስፋት ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ጋር በማያያዝ ነው፡፡ በመሆኑም ከአገራት እድገትና ለውጥ ጋር ትምህርት እድገትም እየተለዋወጠ መጥቷል፡፡ በኢትዮጵያም ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አንስቶ ዘመናዊ ትምህርት እንደተጀመረ ቢነገርም በቤተ እምነቶች አካባቢ ግን ማንበብና መፃፍ ከዚያም በፊት በስፋት ይካሄድ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያመለክታሉ፡፡

ከ1900 በኋላ ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት “ሀ” ብሎ በመጀመሩ ጥቂት ህፃናት የዘመናዊ ትምህርት ማግኘት ችለዋል፡፡ ይህም የተጀመረው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ይህም ትምህርት ቤቱን በዘመናዊ ትምህርት ታሪክ ፋና ወጊ አድርጎታል፡፡ ቀጥሎም እስከ 1925 ዓ.ም ድረስ ባሉት ዓመታት በመላው አገሪቱ ሃያ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ሊከፈቱ ችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች ቁጥር ከስምንት ሺ የሚበልጥ አልነበረም፡፡

በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በትምህርት ዘርፍ በርካታ ሥራዎች የተሠሩበትና ትምህርት ቤቶችም የተስፋፉበት በተቃራኒው ደግሞ በርካቶች ከትምህርት ገበታ በተለያዩ ምክንያቶች የተገለሉበት ዘመን ነበር፡፡

በደርግ ዘመነ መንግስትም የትምህርት ስርዓቱ በኃይለሥላሴ ዘመን በነበረው የቀጠለ ቢሆንም የራሺያ ኮሚኒዝም የተቀላቀለበት ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ደርግ በአገሪቱ የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት በሚያስችል መልኩ ሲሰራ መቆየቱ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ኑሮ በዘዴ፣ እርሻና እደ ጥበብ ነክ ነገሮች በካሪኩለም ተቀርፀው ይሰጡ ነበር፡፡

ከዚህም ባለፈ አንድ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቆ ሲወጣ የቀለምም የሙያም እውቀት እንዲይዝ የሚደርጉ ትምህርቶች ይሰጡ ነበር፡፡ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተምረው የሚወጡ ተማሪዎችም መንግስት በሚመድባቸው ቦታ ሄደው የማገልገል ግዴታ ነበረባቸው፡፡ ይህም የተማረው ሀይል በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ህዝቡን የሚያገለግልበት ዕድል በመፍጠሩ ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል፡፡

የደርግ ዘመነ መንግስት በህዝባዊ ትግል ከወደቀ በኋላ አገሪቱን ማስተዳደር የጀመረው ኢህአዴግ አዲስ የትምህርት ስርዓት ቀርፆ ወደተግባር አስገብቷል፡፡ በዚህም ቀደም ብለው የነበሩት ትምህርቶች እንዲቀሩ አድርጓል፡፡ የመማሪያ መፅሐፍትም መንግስት በሚፈልጋቸው መልኩ የፓርቲውን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም እንዲያስፈጽሙ በሚያስችል መንገድ የተቃኙ በመሆናቸው የትምህርት ጥራት በከፍተኛ ደረጃ እንዲወድቅ አድርጓል፡፡

ከዚህም ባሻገር ብዛት ላይ እንጂ ጥራት ላይ ባለመተኮሩ የትምህርት ጥራት ይበልጥ እንዲዘነጋ አድርጎት ቆይቷል፡፡ ከዚህም ባለፈ የመምህራን ትምህርት አሰጣጥ ትኩረት የተሰጠው ባለመሆኑ ብቁ ባለሙያዎችን ማፍራት አልተቻለም፡፡

**በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በትምህርት ዘርፍ በርካታ ሥራዎች የተሠሩበትና ትምህርት ቤቶችም የተስፋፉበት በተቃራኒው ደግሞ በርካቶች ከትምህርት ገበታ በተለያዩ ምክንያቶች የተገለሉበት ዘመን ነበር**

ስለሆነም በኢህአዴግ ዘመን የነበረውን የትምህርት ስርዓት ለማሻሻል አዲስ ስርዓተ ትምህርት ተቀርፆ ወደ ሙከራ ትግበራ በ2014 ዓ.ም ተገብቷል፡፡ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የአደረጃጀት ለውጥ ተደርጓል፡፡ በዚህም የነበረው አደረጃጀት ቅድመ መደበኛ ሁለት ዓመት፣ አንደኛ ደረጃ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ስድስት ዓመት፣ መካከለኛ ደረጃ ሰባት እና ስምንተኛ ክፍል ሁለት ዓመት፣ እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል አራት ዓመት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ከቅድመ መደበኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚሆን ትምህርት ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡ በዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ደግሞ የሙከራ ትግበራ በተመረጡ 80 ትምህርት ቤቶች የሚካሄድ ይሆናል፡፡

ይሄ አሰራር ቀድሞ የነበረውን የትምህርት አሰጣጥ የሚቀይረው ሲሆን ተማሪዎች በቂ የሆነ እውቀት ይዘው እንዲወጡ የራሱን አሻራ ያሳርፋል ተብሎ ይጠበቃል።እዚህ ጋር መስተዋል ያለበት ነገር አዲሱን የትምህርት ስርዓት በአግባቡ የተረዱ መምህራንን ማብቃት ወሳኝ ነገር መሆኑ ነው፡፡ መምህራን በስነ ምግባርና በእውቀት ማጎልበት ከተቻለ ውጤታማ ተማሪዎችን ማፍራት ይቻላል፡፡ ይህ ስራ ደግሞ ከአዲሱ የትምህርት ስርዓት ይጠበቃል፡፡

በአገሪቱ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች መስከረም ዘጠኝ ቀን 2015 ዓ.ም ተከፍተው የመማር ማስተማር ሥራ ጀምረዋል፡፡ በልዩ ልዩ እና አስገዳጅ ምክንያቶች ሰኞ መስከረም ዘጠኝ ቀን 2015 ዓ.ም ትምህርት የማይጀምሩ ትምህርት ቤቶች እንደመኖራቸውም መጠን ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ማስተማር ሥራ እንዲጀምሩ እየተደረገም ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የትምህርት አጀማመሩ በተሳለጠ መልኩ ለማከናወን ያግዝ ዘንድ 34 ሺህ ትምህርት ቤቶች ለአገልግሎቱ ዝግጁ መደረጋቸውን እና ለዚህም 16 ነጥብ ሶስት ሚሊየን ተማሪዎች መመዝገባቸውን ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ከአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ጋር በተያያዘም የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል አዲሱ ስርዓተ ትምህርት የሙከራ ትግበራ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም በተመረጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2015 ዓ.ም እንደሚጀመር የተጠቀሰ ቢሆንም ስራው ከሙከራ ትግበራነት ባፋጣኝ መውጣት ካልቻለ የተዘበራቀ ትምህርት አሰጣጥ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ለምን ቢባል በሙከራ ትምህርቱን የጀመሩትና ቀደም ብሎ ያለውን እየተማሩ ያሉት ተማሪዎች ወጥ የሆነ እውቀት ስለማያገኙ ነው፡፡

የሙከራ ትግበራ ከሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ መምህራን ስርዓተ ትምህርቱን የማስተዋወቅ የአሰልጣኞች ስልጠና እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን፤ አዲሱ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት በርካታ ደረጃዎችን አልፎ ለሙከራ ትግበራ የደረሰ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር ጠቅሷል፡፡

በስርዓተ ትምህርት ዝግጅቱ ላይ የተመረጡ የመማር ማስተማር፣ የልህቀት ማዕከላት ዩኒቨርሲቲዎች እና ካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ በአማካሪነት መሳተፋቸው ለትምህርት አሰጣጡ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

ይህ ሥርዓተ ትምህርት አገር በቀል እውቀትን፣ ግብረገብነትን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የተላበሰ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በዚህ የሙከራ ትግበራ ወቅት ከመምህራንና ከባለድርሻ አካላት ብዙ ግብዓቶች ተሰብስበው፤ ወላጆችና ሌሎችም አስተያየት እንዲሰጡበት በድረ ገፅ እንዲለቀቅ ተደርጓል። በሙከራ ትግበራው ወቅት የሚመጡ አስተያየቶች ተካተው በ2016 ዓ.ም ወደ ሙሉ ትግበራ ይገባል፡፡ የሚሰጠው ስልጠናም መምህራን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መጽሐፉ እንዲተዋወቁ ይረዳቸዋል።

በአዲሱ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ሌላው ሊተኮር የሚገባው በሁሉም ክልሎች የሚሰጠው ትምህርት ወጥነት ያለው እንዲሆን ማድረግ ላይ ነው፡፡ ቀደም ብሎ በነበረው የትምህርት ስርዓት በክልሎች ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተለያየ በመሆኑ በአንድ ጉዳይ ላይ መግባባት እንዳይመጣ ማድረጉ የሚታወስ ነው። በዚህም ትውልዱ የአገር ፍቅር እንዳኖረው መሰረት ጥሏል፡፡ አሁንም ይህ ሁኔታ እንዳይደገም ማድረግ ይገባል፡፡

በአዲሱ የትምህርት ስርዓት ውስጥ የተጨመሩ የትምህርት አይነቶችን ለማስተማር ብቁ የሆነ መምህር ማፍራት ላይ ትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ጠንክረው መስራት አለባቸው፡፡

በተጨማሪም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም በመምህርነት የሚያሰለጥኗቸው ባለሙያዎች በቂ እውቀት ይዘው እንዲወጡ በአግባቡ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

# የኢሬቻ በዓል የቀደመውን ባህላዊና ትውፊታዊ ሥርዓት ጠብቆ እንዲከበር ጥሪ ቀረበ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**



ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ በፈጣሪና በፍጥረት መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያጠናክር የገዳ ሥርዓት ፍልስፍና አካል በመሆኑ በዓሉ ባህላዊና ትውፊታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ መከበር እንዳለበት ጥሪ ቀርቧል።

የ2015 ዓ.ም የሚከበረውን የሆረ-ፊንፊኔና ሆረ-ሃርሰዴ ኢሬቻ በዓል በማስመልከት አባ ገዳዎች፣ ምሁራንና ወጣቶች በኦሮሚያ ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት በመገኘት 24ኛውን 'የጉሚ በለል' ውይይት አድርገዋል።

ውይይቱ ላይ የተገኙት የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ሁሴን ፈይሶ፣ ኢሬቻ ምስጋና እንዲሁም ምልጃ የሚቀርብበት ስፍራ በመሆኑ በርካታ ታዳሚዎች የሚገኙበት፣ አንድነትና ወንድማማችነት የሚጠናከርበት እንዲሁም በሕዝቦች መካከል መተማመንን በማጎልበት ለአገራዊ አንድነት አስተዋፅኦው የጎላ እንደሆነ ተናግረዋል።

በኦሮሚያ ብልፅግና ጽሕፈት ቤት የጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከድር ማሞ ውይይቱን በማስመልከት ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ፤ ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት፤ ከገዳ ሥርዓት ውስጥ ትልቁ የምስጋና ሥርዓት መሆኑን አስታውቀዋል።

ለዘመናት በርካታ መሰናክሎችን በማለፍ ዛሬ ላይ የደረሰውንና ትውልድ ሲቀባበል የመጣውን ትውፊት በቀደመው ባህላዊና ትውፊታዊ ሥርዓቱ በጠበቀ መልኩ መከበር እንዳለበት ገልፀዋል።

የውይይቱ ተሳታፊ አባ ገዳ ጎበና ሆላ በበኩላቸው፤ የበዓሉ ታዳሚዎች እርጥብ ሳር በመያዝ ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ሌሎች የኢሬቻ በዓልን የማይወክሉ ቁሳቁሶችን እንዲሁም የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ አርማዎችና ሰንደቅ አላማዎችን የሚያመለክቱ ነገሮችን ይዞ መገኘት አያስፈልግም ብለዋል።

ይህም ማኅበረሰቡ በሰላም ወጥቶ በዓሉን አክብሮ እንዲመለስ በጎ አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ ማኅበረሰቡ፣ ወጣቶች እንዲሁም የአገር ሽማግሌዎች ለዚህ መሳካት የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢሬቻ በዓል ከባህላዊ መስህቡ ባለፈ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የበዓሉ ታዳሚዎች በአዲስ አበባና በቢሾፍቱ የሚገኙ በመሆኑ የንግዱ ማኅበረሰብ በዕለቱ የሚያስፈልገውን አገልግሎት በተገቢው ሁኔታ በመስጠት ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባው ከተሳታፊዎች ጥሪ ቀርቧል።

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት 58 ዋና ዋና የኢሬቻ በዓል ሥነ ሥርዓት የሚከናወንበት ስፍራ መኖሩን የገለጹት ተሳታፊዎቹ፣ ምሁራንና አባ ገዳዎች በየአካባቢው ያለውን የኢሬቻ ባህላዊ ሥነ ሥርዓት አጉልቶ በማውጣት ለአገር የቱሪዝም ሀብት እንዲውል የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የባህል አልባሳትን በሰፊው በማስተዋወቅ፣ ባህላዊ ምግቦች፣ እንዲሁም ሌሎች ባህሉን በሚያጎሉ ሥራዎች ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባቸውም ተገልጿል።

# አሸባሪው ትሕነግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ምክንያት የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ምርመራ ሲደረግ እንደነበርም አብራርተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ምርመራው በሰፊው እንዲካሄድ የሚኒስትሮች ግብረኃይል ካቋቋሙ በኋላም ቀደም ሲል የተገኙ የምርመራ ውጤቶችንና ማስረጃዎችን በመያዝ ሰፊ የምርመራ ሥራ ሲሠራ መቆየቱንና የመጀመሪያው ምዕራፍ ምርመራ ሊገባደድ መቃረቡን አቶ ፈቃዱ ገልፀዋል።

ግብረኃይሉ አራት ኮሚቴዎችን አቋቁሞ ምርመራውን ሲያከናውን መቆየቱን የተናገሩት አቶ ፈቃዱ፤ የምርመራና ክስ ንዑስ ኮሚቴ በፍትህ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ሲገመገም እንደቆየና የመጀመሪያው ምዕራፍ ምርመራ ባይጠናቀቅም በርካታ ማስረጃዎች መገኘታቸውን ጠቅሰዋል።

በምርመራ ውጤቱ አሸባሪው ትሕነግ ሒሳብ አወራርዳለሁ በሚል የፈፀማቸው የግድያ፣ አስገድዶ መድፈርና ዘረፋ ወንጀሎች እንደተፈፀሙ መረጋገጣቸውን ተናግረዋል።

መንግሥት የጥሞና ጊዜ ለመስጠት ከትግራይ ክልል በወጣበት ጊዜ የትሕነግ አሸባሪ ቡድን የመከላከያ ሠራዊቱን እግር ተከትሎ በአማራና በአፋር ክልሎች ወረራ በማድረግ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸሙን ገልፀዋል።

አሸባሪው ቡድን ሒሳብ አወራርዳለሁ ብሎ በነዛው ፕሮፖጋንዳ ተመስርቶ በአማራና አፋር ክልሎች የጅምላ ግድያ ስለመፈፀሙ በምርመራው ተረጋግጧል ያሉት አቶ ፈቃዱ፤ በማይካድራ፣ በሰሜን ሸዋ አንፆኪያ ገምዛ ወረዳ፣ በጭና፣ በቆቦ እና በጋሊኮማ የጅምላ ግድያዎች እንደተፈፀሙ የሚያሳዩ ማስረጃዎች በምርመራው ተገኝተዋል ብለዋል።

የጅምላ ግድያዎቹም ሆን ተብሎ እና የአሸባሪው ትሕነግ አመራሮች አቅደውና አመራር ተሰጥቶበት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ማስረጃዎች ማሰባሰባቸውን ገልፀዋል።

እንደ አቶ ፈቃዱ ገለፃ፣ የተቋቋመው ግብረኃይል የምርመራ ውጤቱን ለማግኘት በአማራ ክልል ብቻ የተበዳዮችን ቃል ጨምሮ 9 ሺህ 552 የምሥክሮች ቃል እንዲሁም በአፋር ክልል የ517 ምሥክሮችን ቃል ተቀብሏል። 3 ሺህ 087 የሰነድ ማስረጃዎች በሂደቱ ተደራጅተዋል። 2 ሺህ 599 የተንቀሳቃሽ ምስል እና የፎቶ ማስረጃዎች ተጠናቅረዋል።

በምርመራ ሂደቱ የተገኘው ከፍርድ ውጪ ግድያ ከተፈጸመባቸው ሁለት ሺህ 831 ንጹሃን ዜጎች አብዛኞቹ በሽብር ቡድኑ ሕወሓት መፈፀማቸውንና አንድ ሺህ 315 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን እንዲሁም 472 ሰዎች ላይ ከፍተኛ የኢሰብአዊ አያያዝና ለስቃይ መዳረጋቸውን አቶ ፈቃዱ አብራርተዋል። በተጨማሪም 36 ሰዎች የደረሱበት እንደማይታወቅ በምርመራ ሂደቱ ተረጋግጧል ብለዋል።

ሁለት ሺህ 831 ከፍርድ ውጪ የተፈፀሙ ግድያዎች በአብዛኛው በትሕነግ የተፈፀሙ ሲሆን በሰሜን ሸዋ ዞን ወረዳዎች እና በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ላይ አሸባሪው የሸኔ ቡድን የተሳተፈ መሆኑን በምርመራ ሂደቱ መረጋገጡንም አስታውቀዋል።

ግድያዎቹ በዕቅድ ተመርተው የተፈፀሙ እና ትሕነግ በጦርነቱ ላይ ምንም ተሳትፎ ያልነበራቸውን ነዋሪዎችን ዒላማ አድርጎ የፈፀማቸው መሆናቸውን በሚያሳዩ መረጃዎች ተረጋግጧል ነው ያሉት።

በማይካድራ ስድስት የጅምላ መቃብር እና 229 ሰዎች የሞቱበት ሁኔታም ወደ 267 አካባቢ ምስክሮችን በመቀበል 202 ሰዎች ላይ ክስ ተመሥርቶ በክርክር ሂደት ላይ እንደሚገኝ አቶ ፈቃዱ ተናግረዋል።

ከአሸባሪው ትሕነግ ምርኮኞች በተሰበሰበ ቃልም የጅምላ ግድያው በሥልጠና ጭምር ተካትቶ ሲሰጥ እንደነበር እና የግድያዎቹ ሁኔታም በጎዳና ላይ መሆናቸው፤ አሰቃቂ በሆነ መንገድ መፈፀማቸው እና አንዳንዶቹ ደግሞ በአሰቃቂ ሁኔታ አካልን ቀድሞ በመቆራረጥ የሚፈፀሙ መሆናቸው ለማረጋገጥ መቻሉን አብራርተዋል።

መንገድ ላይ አስከሬን እንዳይነሳ መደረጉ እና አስከሬን ጎዳና ላይ እንደወደቀ እንዲፈርስ መደረጉ በአሸባሪው ትሕነግ አመራሮች በኩል ነዋሪውን ማኅበረሰብ መግደል እና ማኅበረሰቡን ማዋረድ እንደ ግብ ተደርጎ ለመወሰዱ ማረጋገጫ ነው ብለዋል አቶ ፈቃዱ።

እንደ አቶ ፈቃዱ ገለፃ፤ የሚገደሉት የብልፅግና አባል የሚባሉ፣ የአማራ ክልል ልዩ ኃይል አባላት ቤተሰቦች የሆኑ፣ የፋኖ ቤተሰቦች የተባሉ እና የመከላከያ ሰራዊት የቤተሰብ አባል የሆኑ መሆናቸው ደግሞ ግድያው እንዲሁ በአጋጣሚ በአሸባሪው ታጣቂዎች የተገደሉ አለመሆናቸውን የሚያሳይና ግድያው በትሕነግ አመራሮች የተመራ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም በቆቦ ጤና ጣቢያ ቆስለው ሲረዱ የነበሩ 30 የሚሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በተኩስ ሩምታ ተገድለው እዚያው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ እንዲቀበሩ መደረጉ በስሜትና በጊዜያዊ ፍላጎት የመጣ ሳይሆን በዕቅድ መመራቱን ያሳያል ሲሉ ጠቅሰዋል።

በመርሳ ስምንት የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከቆሰሉበት እና በሕክምና እየተረዱ ከነበረበት ተወስደው መገደላቸው እና በኮምቦልቻም ኮማ ውስጥ የነበሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በጥይት ተደብድበው ሕይወታቸው እንዲያልፍ መደረጉ በዕቅድ ስለመሠራቱ ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው ሲሉ አብራርተዋል።

በሌላ በኩል የሽብር ቡድኑ በአማራና አፋር ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በርካታ የአስገድዶ ምድፈር እና ሰብዓዊ ጥቃቶች ማድረሱንም አቶ ፈቃዱ ተናግረዋል። በተጠቀሱት ቦታዎች 2 ሺህ 212 አስገድዶ የመድፈር ወንጀሎች መፈፀማቸውንና ይህ ደግሞ ማኅበረሰብን ማዋረድ ላይ እና ሆን ተብሎ ጥቃት ለማድረስ የታቀደ መሆኑን ማሳያዎች ተገኝተዋል ብለዋል።

የ80 ዓመት እናት በሰሜን ሸዋ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተደፈሩበት እና እናትና ልጅ በጋራ ተደፍረው ልጅ ራሷን ያጠፋችበት ሁኔታ መፈጠሩ በምርመራው መረጋገጡን እንዲሁም በአስገድዶ መድፈር ሂደቱ ሆን ተብሎ የአባላዘር በሽታን ለማስተላለፍ የተዘጋጀ ቡድን እንደነበር በምርመራ ሂደቱ ተረጋግጧል ነው ያሉት።

በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተም 26 ሺህ 334 በላይ ቤቶች መቃጠላቸውንና የ51 ሺህ 887 ንብረት የሆኑ 865 ሺህ 627 ኩንታል አካባቢ የሚጠጋ እህልና ጥራጥሬ መዘረፉን ለአብነት የግብረ ኃይሉ አባል ገልፀዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ትምህርት ቤቶችና የሃይማኖት ተቋማት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ አብራርተዋል።

# የኢትዮ- ጅቡቲ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዚህም መሠረት በዘርፉ ማነቆ ከነበሩ ችግሮች መካከል አንዱ የነበረው የኃይል አቅርቦት ችግር በአሁኑ ወቅት መፈታቱን ጠቁመው፤ በቀጣይም የተቋሙን መዋቅራዊ አደረጃጀት የማሻሻልና አሠራሮችን የማዘመን ሥራዎችን በማከናወን ዘርፉን ይበልጥ ስኬታማ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማህበሩ ከተመሠረተ ገና አራት ዓመታት ያስቆጠረና በርካታ ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም ባለፈው በጀት ዓመት በርካታ ስኬቶችን ማስመዝገቡን ጠቁመዋል። ከእነዚህም ውስጥ በተለይ በቡና ንግድ 98 ከመቶ የቡና ወጪ ጭነት በባቡር የተካሄደ መሆኑን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በመስመሩ ላይ የሚያጋጥሙ የጸጥታ ችግሮችንም በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፍታት የሁለቱ አገራት መንግሥታት በጋራ እየሠሩ እንደሆነ በመጠቆም፤ በአሁኑ የቦርድ ስብሰባ ላይም የሁለቱ አገራት የፌዴራል ፖሊስ አመራሮች ተሳትፈዋል ብለዋል።

የኢትዮ ምድር ባቡር በብዙ ፈተናዎች ውስጥም ሆኖ 2014 በጀት ዓመት አጠቃላይ አገሪቷ ከአካሄደችው የወጪ እና ገቢ ጭነት ውስጥ 11 ከመቶ መሸፈኑንም ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ከመቋቋሙ እና የኢንዱስትሪ ፓርኮችም በስፋት እየተሠሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡር በቀጣይ ለኢኮኖሚያዊ እድገቱ የሚኖረው ሚና የላቀ እንደሚሆን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል። ይህንን ለማሻሻልም ከፍተኛ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው ብለዋል።

የኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡር አክሲዮን ማህበር በ2014 በጀት ዓመት ከ2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ የሎጅስቲክ ወጪ ማዳኑንም ተናግረዋል።

ማህበሩ እ.አ.አ በ2017 ሚያዝያ ወር ላይ በ500 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማቋቋሚያ ካፒታል በኢፌዴሪ እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥታት የሁለትዮሽ እንዲሁም በባለ አክሲዮኖች ስምምነት የተቋቋመ መሆኑን ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

ትናንት በተካሄደው የቦርድ አመራር አባላት ስብሰባ ላይ ከሁለቱ አገራት የተውጣጡ የቦርድ አመራር አባላት እና የፖሊስ አመራሮች ተገኝተዋል።

# የሸኔ አባላት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሽሮና በርበሬ ሳይቀር ዘርፏል።

አሁንም በተመሳሳይ ትህነግ እና የግብር አጋሩ ሸኔ በፈጸሙት ሦስተኛ ዙር ወረራ ተመሳሳይ ጥፋት እየፈጸሙ መሆናቸው ይታወቃል። ይህንንም በሠነድ ሳይቀር አስደግፈው እየሠሩበት መሆኑን ከተጋለጠው ምስጢራዊው ሠነድ መረዳት ተችሏል።

ከባቲ ተነስተው የሽብር ቡድኑን የተቀላቀሉት የሸኔ አባላት ከሌላኛው የጥፋት ኃይል ትህነግ ጋር ተሰልፈው ሲዋጉ እንደነበር በግንባር ለሚገኙት የኢፕድ ዘጋቢዎች ተናግረዋል።

ትህነግ ባቲ ከተማን ከወረረ በኋላ ተሸንፎ አካባቢውን ለቆ ሲሄድ ከግብረ አበሩ ሸኔ ጋር በመተባበር ተዋጊዎችን መመልመሉን እነዚሁ እጃቸውን የሰጡት ታጣቂዎች አስረድተዋል።

በኋላም ወደ ትግራይ በማምራት ለወራት ወታደራዊ ስልጠና መውሰዳቸውን የገለጹት ታጣቂዎቹ፤ በመጨረሻም ከትህነግ አመራሮች የቀረበላቸውን ትጥቅ ይዘው አፋርና አማራ ክልል ላይ ወረራ ሲፈጸም መሳተፋቸውን ነው የገለጹት።

አላማ ለሌለው ጦርነት ሕይወታቸውን መገበር እንደሌለባቸው የተረዱት የሽብርተኛው ሸኔ አባላት ግን መሹለኪያ መንገድ በማመቻቸት ለመከላከያ ሠራዊት እጃቸውን መስጠታቸውን ተናግረዋል።

ሠራዊቱም በተገቢው መንገድ እየተንከባከባቸው መሆኑን እጃቸውን የሠጡት የሽብር ቡድኑ አባላት ገልጸዋል።

አብዱ አሊ መሐመድ ከእነዚህ የሸኔ ታጣቂዎች መካከል አንዱ ነው።

አብዱ ትህነግ ባለፈው አመት የአማራና አፋር ክልል አካባቢዎችን በወረራ ሲይዝ ከቡድኑ ጋር የተቀላቀለ የሽብርተኛው ሸኔ አባል ነው።

ትህነግ በመከላከያ ሠራዊት ብርታት ከያዛቸው ቦታዎች ሲለቅ ከሚሴን ከተማ ለቆ መሄዱንና በከሚሴ የመንግሥት ሠራተኛ እንደነበር የተናገረው አብዱ፤ ከቡድኑ ጋር ወደመቀሌ ማምራቱን አስረድቷል።

በትግራይም ከበርካታ የሸኔ አባላት ጋር ስልጠና መውሰዱን በመግለጽ፤ ትህነግ ለሦስተኛ ዙር ታጣቂዎቹን ሲያሰማራ እርሱንና ጓደኞቹን አብሮ ወደ ጦርነት ማሰማራቱን ተናግሯል።

በመጨረሻም እጁን ለመከላከያ ሠራዊት ከሰጠ በኋላ የጥፋት ቡድኖቹ ሸኔና ትህነግ መጠቀሚያ በመሆኑ መጸጸቱን ገልጿል።

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከአገር ቤት ይጀምራል

በተሰናበትነው ሳምንት በቀጥታ ግንኙነት ወይም ተያያዥነት ያላቸው የማይመስሉ ለአመታት የቀጠሉ ሶስት ኩነቶች ተከናውነዋል። ነጥቦችን አገጣጥሞ ለመመልከት ለሞከረ ግን ወደ አንድ ምስል ይመራሉ። የመጀመሪያ ሽብርተኛውና ባንዳው ሕወሓት ለ3ኛ ጊዜ ከነሐሴ አጋማሽ ወዲህ እስከ ዛሬ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የከፈተው የክህደትና የውክልና ጦርነት ሲሆን ፤ ሁለተኛው በመንግስታቱ ድርጅት (ተመድ) የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በአገራችን ላይ ያወጣው ፍርደ ገምድልና አሳፋሪ ዘገባ ነው፤ ሶስተኛው በአፋር ክልል ጠቅላይ ሚንስትሩ በኩታ ገጠም የለማ የጥጥ እርሻ መጎብኘታቸው ነው ።

ሽብርተኛውና የእናት ጡት ነካሹ ሕወሓት የጋላቢዎችን የእነ ግብጽን አገርን የማተራመስና የማፍረስ ተልዕኮና ስምሪት ተቀብሎና እኔ እንደ ብረት ቀጥቅጨ የማልገዛትና የማልዘርፋት አገር ትፍረስ ከሚል ግብዝነቱ ጋር አጃምሎ ሉዓላዊነታችንና ነጻነታችን ለመናድ በሕዝባዊ ማዕበል የከፈተብንን ወረራ፤ ጀግናው የጥምር ኃይል እና የአማራ፣ የአፋርና መላው የኢትዮጵያዊ ሕዝብ ደግሞ በአስተማማኝ ደጀንነት እየመከተው ይገኛል። ይሄን የውክልና ጦርነት ከእውነት አምላክ ጋር በቅርብ በአንጸባራቂ ድል እንደመድመዋለን ብዬ አምናለሁ።

በሉዓላዊነትና በነጻነታችን ላይ የተከፈተው ጦርነት ሌላው ግንባር በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲውና በሚዲያው የተከፈተብን የተቀናጀና የተናበበ ጦርነት ነው። ባለፉት ሶስትና አራት አመታት አገራችን የተፈጥሮ ሀብቷን በማልማቷና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር በመንቀሳቀሷ ደርዘን ጊዜ በመንግስታቱ ድርጅትና በጸጥታው ምክር የተከሳሽ ሳጥን ቆማለች። ራሱን ዓለም አቀፍ ሚዲያ ብሎ የሚጠራው ኃይልም በሀሰተኛ ወሬና ሆን ተብሎ በተዛባ መረጃ ሊፈታት ሌት ተቀን ሰርቷል። እየሰራም ነው ። ባለፈው ሳምንት በሽብርተኛው ሕወሓት ተደርሶ፤ በመንግስታቱ ድርጅት የሰብዓዊ ኮሚሽን ስም የወጣው እንቶፈንቶ ዘገባ የፖለቲካዊ ዲፕሎማሲው ሌላ ቅርሻ ነው።

ይሄን አሸባሪ የማዳን መጋጋጥ መላው ዜጋ በተለይ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኘው ትውልደ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊ ከወዳጆቹ ጋር ሆኖ እየመከተው ይገኛል። ሆኖም በአሳዛኝ ሁኔታ በዲፕሎማሲው፣ በሚዲያውና በተግባቦቱ ዘርፍ ዛሬም እውነትንና ፍትሕን ታቅፈን ተከላካይና አስተባባይ መሆናችን ቀጥሏል። አጀንዳ ተቀባይ እንጂ አጀንዳ ቀርጸን ወደፊት ማምጣት አልቻልንም። አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም በሚል ተስፋ የመቁረጥ አባዜ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡንና ዓለም አቀፍ ሚዲያውን ለከሀዲውና ለአሸባሪው ሕወሓት በፈቃዳችን ስለ ለቀቀንለት ዛሬም ከጀርባ እየተወጋን ነው። ሰሞነኛ የመንግስታቱ ድርጅት የሰብዓዊ ኮሚሽን ባለሙያዎች ዘገባ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

የአገር ውስጥ ሁለንተና አቅማችንን እስክንገነባ ድረስ ከሴናተሮች፣ ከኮንግረስ አባላት፣ ከአውሮፓ ሕብረት፣ ከሚዲያዎችና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚያግባባንና የሚያገናኝ (ሎቢ)ልንቀጥር ይገባል። በነገራችን ላይ የምዕራባውያን በተለይ የአሜሪካ ሚዲያ፣ ኮንግረስ ፣ ሴኔትና ሌሎች ተቋማት ያለ ሎቢስት አይታሰቡም። አይደለም የእኛ የንባዳዎቹ ጉዳይ የአሜሪካኖች የራሳቸው ጉዳይ ያለ አግባቢ(ሎቢስት) ስንዝር ፈቀቅ አይልም። ከእያንዳንዱ ሕግ ፣ ፖሊሲና ውሳኔ ጀርባ እልፍ አእላፍ ሎቢስቶች አሉ።

በዋሽንግተን ዲሲ ብቻ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ፤ በአውሮፓ ሕብረት መቀመጫ ብራስልስ ደግሞ እስከ 30ሺህ የሚደርሱ ሎቢስቶች ይርመሰመሳሉ። ከእያንዳንዱ ግዙፍ ኩባንያና ማህበራት ጀርባ ሎቢስት አለ። ከሕዳሴው ግድብና ከአሸባሪው ሕወሓት ጀርባ ያሉ ኃይላት ነገም አይተኙልንምና ሎቢስት መቅጠር ግድ ይለናል። ምንም እንኳ ለወጪ የሚዳርገን ቢሆንም፤ በፈጠራ ወሬና በተዛባ መረጃ እየተፈጠረብን ካለው ጫናና እየጠለሸ ካለው ገጽታችን ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የማይባል ነውና ሎቢስት ሊኖረን ይገባል።

ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳዩ ስመለስ፤ ዘላቂው መፍትሔ ምዕራባውያን ድህነታችንና ኋላቀርነታችንን መያዣ አድርገው ዝቅ አድርገው እንዳያዩን፤ ከፍ ሲልም በእርዳታና በብድር ሰበብ በነጻነታችንና በሉዓላዊነታችን ላይ እንድንደራደር እጃችን ለመጠምዘዝ የሚደረገውን ጥረትና ጫና ለመቋቋም የድህነትንና የኋላቀርነትን ቀንበር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መስበር አለብን። የግብርናውን ፣ የኢንዱስትሪው ፣ የአገልግሎት ዘርፉን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የድህነትንና የኋላቀርነትን ቀለበት ሰብረን የመውጣት ጉዳይ ለነገ የሚተው ጉዳይ አይደለም ።

አስተማማኝ የስራ ዕድል መፍጠር ፤ የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነትን ከመቀነስ ጎን ለጎን ደግሞ የዴሞክራሲ፣ የደህንነትና የጸጥታ ተቋማትን መገንባት፤ የሕዝብን አንድነት የሚሸረሽሩ ፖለቲካዊ ሴራዎችንና ደባዎችን ተቆራርጦ መታገል፤ ብልሹ አሰራሮችንና ሙስናን ፤ ጽንፍ የረገጠ ብሔርተኝነትን ፤ ወዘተረፈ ማስወገድ ፤ ውስጣዊ ለቀውስ ተጋላጭነትን ከመቀነስ ባሻገር እንዳለፉት ሶስትና አራት አመታት ያሉ ያላባሩ ጫናዎችን ለመመከት ጉልበት ይሆናሉ። ከውጭው ጫና ይልቅ እነዚህን የቤት ስራዎቻችንን አበክረን ባለመከወናችንና ባለመስራታችን የሚመጣብን አደጋ የከፋ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ይበል የሚያሰኙ ናቸው። መንግስት ምንም እንኳ ወደ ስልጣን ከመጣበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በየአቅጣጫው ዘርፈ ብዙ የጥቃት ግንባሮች ተከፍቶበት ፋታ ባያገኝም ተስፋ የሚጣልባቸውን ተግባራት አከናውኗል።

ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን በአፋር ክልል እየለማ ያለ የጥጥ እርሻን በጎበኙበት ወቅት፤ " አባቶቻችን ደማቸውን አፍስሰው ፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ያጎናጸፉንን ሉዓላዊነትና ነጻነት በላባችን ማስከበር ካልቻልን ልናጣው እንችላለን። " በማለት ድሀና ተመጽዋች አገር ነጻና ሉዓላዊ ሊሆን እንደማይችል አጽንኦት ሰጥተዋል። አመቱን ሙሉ የሚገማሸሩ ወንዞችን ፣ ሊታረስ የሚችል ሰፊ ለም መሬትንና አምራች የሰው ኃይሉን አቀናጅተን በአመት ሁለትና ሶስት ጊዜ በማምረት በምግብ እህል ራሳችንን ችለን ለፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚተርፍና ለውጭ ገበያ የሚቀርብ አምርተን ከድህነትና ከኋላቀርነት ካልተላቀቅን አያት ቅድመ አያቶቻችን መስዋዕት ሆነው ያቆዩን ነጻነትና ሉዓላዊነት ሙሉ ሊሆን አይችልም ።

ለዚህ ነው የለውጥ ኃይሉም ሆነ የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ መንግስት ወደ ኃላፊነት እንደመጣ ድፍረት የተስተዋለባቸውን ማሻሻያዎችን ያደረገው በተለይ የሕዳሴው ግድብ ላይ ተደቅኖበት የነበረን አደጋ የመቀልበስ ፤ የአረንጓዴ አሻራ ፣ የኩታ ገጠም እርሻ ፣ የበጋ ስንዴ ፣ የሜካናይዜሽን ግብርናን ፣ ወዘተረፈ በመተግበር የሚጨበጥ ለውጥ ያመጣው። ሕዳሴውን ከለየለት ከሽፈት ታድጎ ለዚህ ስኬት የበቃው። ከባለፈው አመት ጀምሮ ስንዴን ከውጭ ማስገባት አቁሞ ራሱን የቻለው ፤ በዚህ አመት ደግሞ ወደ ውጭ ለመላክ ያቀደው። ይህ ስኬት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን አካልና መደላድል ነው ። ውስጣዊ ድሎቻችን ለውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን አቅም ናቸው። ከፍ ብዬ የጠቀስኳቸው ሶስቱ ኩነቶች ወደዚህ የሚያደርሱ ናቸው ።

አንድ ምስል ይከስታሉ ያልሁትም ይሄን ነው። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጉምቱ አሜሪካዊ ሪቻርድ ሀስ፤ " የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከአገር ቤት ይጀምራል ፤ "/ FOREIGN POLICY BEGINS AT HOME :..."በሚል መጽሐፉ ይሄን ይተነትናል። ጠቅላይ ሚንስትሩና መንግስታቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከአገር ውስጥ እንደሚጀምር አበክረው ተገንዝበው እየሰሩ ያሉት ለዚህ ነው። ለዛሬ መጣጥፌ መግፍኤ ወደ ሆነው ወቅታዊ ጉዳይ ስመለስ፤ አበውና እማው ነገርን ከስሩ ፣ ውሃን ከጥሩ እንደሚሉት ፤ የመንግስታቱ ድርጅት ሰሞነኛ አሳፋሪና ወራዳ ተግባር የሚጀምረው ኢፍትሐዊና በእኩልነት ላይ ካልቆመው አመሠራረቱ ነው። የCNN የGPS አዘጋጅና የ"ዋሽንግተን ፖስት"አምደኛ የሆነው ፋሪድ ዘካሪያ ፤"THE FUTURE OF FREEDOM: ILLIBERAL DEMOCRACY AT HOME AND ABROAD" በሚል ባደረሰን ማለፊያ በተሰኘው መጽሐፉ፤ "የተባበሩት መንግስታት አሰራር የጨረር የኃይል አሰላለፍ ወካይ ነው።

የመንግስታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባላት ከ70 አመታት በፊት የ2ኛውን የዓለም ጦርነት በአሸናፊነት የደመደሙ አገራት ናቸው ። አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ራሽያና ቻይና። ምክር ቤቱ በአለማችን በኢኮኖሚያቸው 3ኛና 4ኛ ደረጃ የሚገኙትን ጃፓንና ጀርመንን፣ ባለትልቁ ዴሞክራሲ የሆነችውን ሕንድ፣ ላቲን አሜሪካንና አፍሪካን ያገለለ ነው። "ይለናል ። "እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው፤ ግን አንዳንድ እንስሳት ከሌሎች ይበልጥ እኩል ናቸው።"እንደሚባለው የጸጥታው ምክር ቤትም በእነ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ብርቱ ተጽዕኖ ስር የወደቀ ነው። ስለሆነም በመንግስታቱ ድርጅት ስር የሚንቀሳቀሱ ተቋማት የሰብዓዊ መብት ምክር ቤቱን ጨምሮ የእነዚህን አገራት ፍላጎት ማስፈጸሚያ እንጂ ገለልተኛና ነጻ ተቋማት አይደሉም። የሰሞኑን በአገራችን ላይ የወጣው ፈራጅና ወንጃይ ሪፖርት የዚህ ፍላጎት ነጸብራቅ ነው። ከዚህ ጀርባ ደግሞ አይደለም ዛሬ አባይን ገድበን ምንጊዜም ተኝታልን የማታውቀው የግብጽ እጅም አለበት።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በስሚ ስሚና የጌቶቻቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም አካሄድሁት ባለው "ምርመራ"፤ ከሽብርተኛው ሕወሓት ጭፍራዎች ባገኘው ሀሰተኛና የተዛባ መረጃ ተመስርቶ በጅምላ የጦር ወንጀል ፈጽማችኋል እያለን ነው። በሰሜን ዕዝ ላይ ትውልድም ታሪክም ይቅር የማይሉት ክህደት የፈጸመው፤ ከአንድም ሁለት ሶስት ጊዜ ጦርነት የከፈተው፤ በቀደሙት 27 አመታት ደግሞ ጎልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍና ሰቆቃ የፈጸመው ዘራፊ ከሀዲና አሸባሪው ሕወሓት ተቀምጦ የፌዴራል መንግሥት ኃይሎች በሰብዕና ላይ የተፈጸመ ወንጀል አከናውነዋል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት አግኝቻለሁ ሲል ይሄው ኮሚሽን ተብዬ ልግጫ ይዟል፡፡ ከጅምሩ ገለልተኛ ያልሆነውና አበክሮ ድምዳሜ ላይ ደርሶና ወስኖ አካሄድሁት ያለው ምርመራ እንደጠበቅነው ነጻና ገለልተኛ ያለሆነ ሪፖርት በመፈብረክ ከሽብርተኛው ጎን ቆሟል።

መች በዚህ ያቆምና ኮሚሽኑ በሁለት ወራት ውስጥ በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ባደረግሁት ምርመራ፤ በጦርነቱ ውስጥ የተሳተፉት የፌዴራል መንግሥት፣ የትግራይ ኃይልና የኤርትራ መንግሥት የንፁሃን ግድያ፣ ወሲባዊ ጥቃትና ሰብዓዊነትን የማዋረድ ወንጀሎችን እንደፈጸሙ አምኛለሁ ይለንና ወረድ ብሎ ደግሞ ሕወሓት ነጻ ያወጣና ውንጀላውን መንግስትና ኤርትራ ላይ ይደፈድፋል። ይሄ ነውር ጌጡ የሆነ ኮሚሽን ወረድ ብሎ ደግሞ፤ ራሱ የመንግስታቱ ድርጅትና ሌሎች ተቋማትን በሚጻረር መልኩ፤ የፌዴራል መንግሥት ‹‹የዜጎችን ረሃብ እንደ ጦርነት መሣሪያ›› ተጠቅሟል ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት እንዳገኘ በሀሰት ይወነጅላል። ይሄን ሁሉ የውንጀላ ዶፍ የሚያዘንብብን እንግዲህ በሁለት ወር ለብለብና በሁለት ባለሙያዎች ነው። የምርመራው ሒደት ተቀባይነት ካላቸው ስነ ዘዴዎች ጋር የሚጣረስ፤ በመንግስታቱ ድርጅት ቻርተር ከተቀመጠው የገለልተኝነት መርሕ ጋር የሚቃረን ነው።

ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፤ ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በኢትዮጵያ ላይ አካሂጄዋለሁ ያለው "የምርምራ ሪፖርት" የተሟላ እንዳልሆነ ፤ ከመረጃ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ያጋጠመውን ተግዳሮት እንደሚገነዘበው ኮሚሽኑ በመጥቀስ "ሪፖርቱ" ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን እና የጦር ወንጀሎች ተፈጽመዋል ለማለት ፍጹም የተሟላ እንዳልሆነ እቅጩን ነግሮታል ። በ"ሪፖርቱ" በአፋር ክልል ላይ ተፈጽሟል ስለሚባለው የከፋ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ወንጀል ምንም አለማለቱ አንዱና ትልቁ የሪፖርቱ ጉድለት መሆኑን ፤ በአንጻሩ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር በመሆን በጥምረት ያካሄዱት ምርመራ ውጤት የተሟላና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ምክር ቤትም ተቀባይነት ያገኘ፤ ምርመራው ገለልተኛና ግልጽነትን ባሰፈነ መልኩ የተሰራ መሆኑን በመጥቀስ ምስጋና ያተረፈ እንደሆነ ያስታውሳል ።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በጋራ በተሰራው የምርመራ ውጤት ላይ ለተደረሰባቸው ግኝቶች የተቀመጡ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በማሳወቅ በዘወርዋራ ይህን የጨረባ ሪፖርት እንደማይቀበለው ይፋ አድርጓል። በቀደመው ሪፖርቱ መሰረት በሁሉም ወገኖች ያሉ ሃይሎች ምክረ ሀሳቡን ተቀብለው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀረበው ኮሚሽኑ ፤ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ሚኒስትሮች የተካተቱበት ግብረ ሃይል በማቋቋም የሄደበትን ርቀት እንዲያጠናክር ጠይቋል። ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽንም የጋራ ምርመራ ውጤቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ እንዲደግፍና ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አቅርቧል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንም ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በተቀመጠው የትብብር ማዕቀፍ ውስጥ ለመተባበር ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ ገልጿል። ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በሰሜኑ ኢትዮጵያ ያለውን ጉዳይ በጥንቃቄ ሊያይና ሊመረምር እንደሚገባው በማሳሰብ፤ ሁሉንም ተጎጂ የህብረተሰብ ክፍሎችና ክልሎች ፍትሀዊ ሆኖ ሳያዳላ ሊመለከት እንደሚገባው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምክረ ሀሳብ ሰጥቷል ።

ሕዳሴያችንን የሚያቆም ምንም አይነት የምድር ኃይል የለም !!!

# የሕይወት ገጽታ

# ከአንጋፋ ጋዜጠኞች ጀርባ ያሉት - ጠንካራው ጠንክር

እፀገነት አክሊሉ

ጉራጌ ብቻውን አያድግም፤ ሲያደግም አንተን ይዞህ ያድጋል።አገር ሆኖ ሰፍቶ ያለውን አካፍሎ ከሌለው ላይ አጉርሶ ወንድም እህት አባት ሆኖ አብሮህ ያድጋል።ከታዋቂዎቹና አንጋፎቹ ጋዜጠኞች ጀርባ አንድ ገመና ሸፋኝ ታታሪ ወጣት ነበር።አሁን ያ ወጣት የአንድ ታዋቂ የጉራጌ ባህላዊ ሬስቶራንት ባለቤት ሆኗል።

አንጋፋ ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ መድረክ ላይ የእሱ ውለታ እንዳለባቸው ሲናገሩ ማድመጥም የተለመደ ነው።በእነሱ ትዝብት እንደውም የዚህ ታታሪ ወጣት ውለታ ተከፍሎም የሚያልቅ አይደለም።ሁሌም በየመድረኩ ስለዚህ ወጣት ሲጠየቁ ወደኋላ በመመለስ የሆነውንና ይደረግ የነበረውን በምን ሰዓት ምን ዓይነት ውለታ ይውልላቸው እንደነበር መናገር የሁሉም ደስታ ነው። ውለታውን ሲያወሩ ደግሞ ትልቅ አክብሮትን ፍቅራቸውም ከፊታቸው ላይ የሚነበበው ብዙዎቹ ላይ ነው፡፡

ወጣቱ ጠንክር ቴኒ አሁን ላይ በጥረት የአንድ ታዋቂና ትልቅ የጉራጌ ሬስቶራንት(ቶቶት) ባለቤት ሆነዋል።ጠንክር እዚህ ለመድረሱ ብዙ ጥረዋል፤ ለፍተዋል፤ ከሊስትሮነት ተነስተውም ያሰቡበት ደርሰዋል።በዚህ የስራና የኑሮ ውጣውረድ ጊዜ ውስጥ ደግሞ በርካቶች ተቸግረው እንዳይቀሩ ባላቸው አቅም እያበደሩም እየሰጡም ተስፋ ሆነዋቸዋል።ይህንን ስራቸውን ደግሞ ብዙዎች ይመሰክሩላቸዋል፡፡

ታዋቂውና አንጋፋው ጋዜጠኛ አለምነህ ዋሴ ስለእሳቸው ሲናገር ከሰማሁት ውስጥ "ጠንክር ማለት የልብ አውቃ ውስጥ አዋቂ ደራሽ ነው፤ ጠንክር ካለ ችግር የለም፤ ባሻህ ሰዓት ያበድርሃል ደመወዝ ስትቀበል ጠብቆ ያስከፍልሃል" ነበር ያለው፡፡

ሌላው አንጋፋ ጋዜጠኛና የማስታወቂያ ስራ ባለሙያ ሳምሶን ማሞ ደግሞ "ምን ጊዜም ሲቸግረኝ ቀድሜ የማደርገው ነገር ጠንክር በስራ ቦታው ላይ መኖሩን ማረጋገጥ ነው። ምክንያቱም ጠንክር ካለ አበዳሪ አለ፤ ከዛ ችግር ይወገዳል ማለት ነው " እያለ ስለጠንክር የክፉ ቀን ወዳጅነት ፈጥኖ ደራሽነት ይናገራል። እነዚህ ብቻም አይደሉም የትልቁ ኢትዮጵያ ሬዲዮ የስራ ባልደረቦች አብዛኞቹ የጠንክር ጥገኞች ነበሩ ቢባል ምንም ማጋነን አይሆንም። ይህ ወጣት ጋዜጠኞቹ የመንግስት ደመወዝተኛ ሆነው እሱ ደግሞ እነሱን ጨምሮ የሌሎች አላፊ አግዳሚዎችን ጫማ በመጥረግ ከሚያገኙት ገቢ እንዳይቸግርቸው ያበድሯቸው የነበረ መሆኑ ነው ትልቁ ሚስጥሩ፡፡

ለዚህ የማይዘነጋ ውለታቸው ደግሞ እንኳን ሰዎቹ የኢትዮጵያ ሬዲዮም አልዘነጋውም። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ ሬዲዮ ጣቢያው የተመሰረተበትን 85ተኛ ልደት በዓሉን ሲያከብር ጠንክር ቴኒን የጋዜጠኞቻችን ባለውለታ በማለት በይፋ ማመስገኑ ነው።

ኢትዮጵያ ሬዲዮ ላይ ብዙ ትዝታ አለኝ የሚሉት አቶ ጠንክር "......አገር ቤት ሆኜ ሬዲዮ ስሰማ ጋዜጠኞቹ ይመስሉኝ የነበረው ቦታ ጠቧቸው የሚጨናነቁ ሰዎች አልያም ደግሞ ሰይጣኖች ነበር፤ ነገር ግን ምነው ከእነዚህ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ አልም ነበር፤ የሕይወት አጋጣሚ ሆኖ ግን እኔ ከአገሬ በመጣሁ በሶስተኛው ወሬ ስራ የጀመርኩት የኢትዮጵያ ሬዲዮ በር ላይ ሆኖ አረፈው" ይላሉ፡፡




«ስራ በጀመርኩ በሶስተኛ ወሬ ደግሞ ብርሃኑ ገብረማርያም ቃለምልልስ አድርጎልኛል።እዛ በር ላይ ጫማችንን ይጠርጋል ብለው እንዳቸውም ንቀውኝ አያውቁም፤ እንዲያውም በጣም ያከብሩኛል፤ ሰርግ ይጠሩኛል፤ አራስ እመርቃለሁ፤ የተቸገረ እረዳለሁ፤ የሌለው ይበደራል፤ ሲያገኝ ይመልሳል በጠቅላላው በጣቢያው ሰራተኞች ተወድጄ ተከብሬ እንደ አንድ የስራ ባልደረባቸው አክብረውኝ ነው እዚህ ያደረሱኝ» በማለት ጠንክር መነሻቸውን ያስታውሳሉ፡፡

ጠንክር ቴኒ ከወይዘሮ አጸደ ተስፋዬና ከአቶ ቴኒ ጉያ አብራክ በጉራጌ ዞን ቸሃ ወረዳ ነው ወልደታቸው። ብላቴናው ጠንክር አገር ቤት እያሉ እንደ እኩዮቻቸው ከብት ጠብቀዋል፤ ጭቃ አብኩተው ከእኩዮቹ ጋር ተጫውቷል ፤ ብቻ በአገር በወንዙ ለልጅ የሚሆኑ ነገሮችን ሁሉ አከናውነዋል።ጠንክር በአገር ቤት ከእኩዮቹ ጋር ከሚያደርጉት መስተጋብር ቤተሰቦቻቸው ለማገዝ ላይ ታች ከሚለው ስራ አረፍ ሲሉ ደግሞ ልማዳቸው የነበረው ሬዲዮ ማድመጥ ነበር።ብቸኛ የነበረውን የኢትዮጵያ ሬዲዮ አብዝቶ ከማዳመጥ የተነሳም የሰዎቹ አድናቂ እንዲሁም ብተዋወቃቸው እያሉ ዘወትር የሚመኙ ወጣትም ነበሩ፡፡

ጉራጌ ስራ ልምዱ ለውጥም ህልሙ እንደመሆኑ አብዛኛው የጉራጌ ማህበረሰብ አገር ቤት የሚቆየው ጫንቃው ለስራ ዝግጁ እስከሚሆን ድረስ ብቻ ነው። ጠንክርም በአገር ቤት ለመቆየት የቻሉት እንደ እኩዮቹ ወይም የአገሩ ልጆች ጫንቃቸው ስራን መሸከም እስከሚችል ጊዜ ብቻ ነበር።ለስራ መድረሳቸውን እርግጠኛ ሲሆን ግን በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ማምራትና ስራ ሰርቶ ራሳቸውን መቻል ብሎም መለወጥ እንዳለባቸው በመወሰን አዲስ አበባ ገቡ፡፡

ገና በዛ ለጋ እድሜያቸው ሰፊዋን አዲስ አበባ ሲቀላቀሉ ዛሬ ላይ ያለው ማንነት ይመጣል ብለው ባያስብም ጠንክሮ ከተሰራ ግን ትልቅ ደረጃ እንደሚደርስ ጠንቅቆ ያውቁም ነበር። በመሆኑም

**ስራ ወዳዱ የብዙዎች ገመና ከታች የሆኑት አቶ ጠንክር ምን ቢያምራቸው ገንዘብ ማጥፋት ላይ ቁጥብ ናቸው።በዚህም ሲስትሯቸውን ብሎም ሱቅ በደረቴያቸውን እንዲሁም ለሚልኳቸው ሁሉ እየተሳኩ አልበላም፤ አልጠጣም፤ አልዘንጠም ብለው ባጠራቀሙት ገንዘብ ምግብ ቤት የመክፈት ፍላጎት አደረባቸው**

አዲስ አበባ ገብቶ የሊስትሮ ሳጥኑን አንስቶ ስራን ሀ ብሎ የጀመረው ድሮ ይመኘው ከነበር የሬዲዮ ጋዜጠኞች መዋያ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ (ከቀድሞው ማስታወቂያ ሚኒስቴር ) በራፍ ላይ ሆነ፡፡

አቶ ጠንክር እየሰሙ ካደጉት ጣቢያ በራፍ ላይ ለእግራቸው ጫማ ሳያደርጉ የሰዎችን ጫማ ማሳመር ጀመሩ።በዚህ ውስጥ ልጅነታቸው ብሎም የገጠሩ ኑሯቸው ተደማምሮ ለስራው እንግዳ ለአገሩ ባዕዳ ቢሆኑም የሰዎች ካልሲ እያበላሹ፤ ቀለም እያባከኑና አንዳንድ ተግሳጾች እየደረሱባቸውም ቢሆን ስራቸውን በትጋትና በብቃት ማከናወኑን ግን ተያያዙት፡፡

ስራ ቢበዛባቸውም በሰሩት ገንዘብ ገቢ ቢያገኙም አገር ቤት ሆነው የጀመሩትን ትምህርት ከመማር ግን ያገዳቸው ነገር የለም፤ ምክንያቱም ገና ከጅምራቸው መድረሻቸው የታያቸው ብልህ ወጣት ስለነበሩ።በዚህም ቀን ቀን በ15 ሳንቲም የሰዎችን ጫማ ሲንከባከቡ ብሎም እዚህም እዚያም ሲላላኩ ይውሉና ማታ ደግሞ ለነጋቸው የሚሆናቸውን ሰንቅ ለማግኘት ከአስኳላው ዘልቀው እውቀትን ሲቀስሙ ያመሻሉ። ባለራዕይው ወጣት ጫማ መጥረግ ብቻውን ያሰቡበት እንደማያደርስ የተረዱም ይመስላሉ። በመሆኑም ከጫማ መጥረግ ስራቸው ጎን ለጎን ሌላ ስራንም መፍጠር እንዳለባቸው አሰቡ፤ በዚህም እዛው ጫማ የሚጠርጉባት ጥግ ላይ እንደ ሶፍትና ማስቲካ ያሉ ነገሮችን በመያዝ ሱቅ በደረቴ አይነት ንግድን ጀመሩ፡፡

ነገን ብሩህ ለማድረግ ዛሬ ላይ ጠንክሮ መስራትን አላማቸው ያደረጉት አቶ ጠንክር ሁለቱንም ስራቸውን በትጋት እየሰሩ የማታ ትምህርታቸውንም አጠናክረው እየተማሩ ለስምንት ያህል አመታት በስኬት አሳለፉ።በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ደግሞ ከላይ እንዳነሳነውም እሳቸውም እንደሚናገሩት በተለይም ለማስታወቂያ ሚኒስቴር (የኢትዮጵያ ሬዲዮ )ጋዜጠኞችና ሰራተኞች ለችግራቸው ፈጥኖ ደራሽ አለሁ ባይ በመሆን ብዙ ውለታን ውለዋል።ይህ አለኝታነታቸው ደግሞ በተቋሙ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያሰጣቸው ከመሆኑም በላይ በሰራተኞቹ ዘንድ እንደ ወንድም፤ እንደ ቤተሰብ እንዲታዩ በሃዘን በደስታውም አብረው እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

የሊስትሮ ስራ፣ ሱቅ በደረቴ እንዲሁም የማታ ትምህርት በዛብኝ ያላሉት ጠንካራው ጠንክር ከእነዚህ ሁሉ ስራዎች ጎን ለጎን ሰዎች ከምግብ ጀምሮ የሚፈልጉትን ነገር ከዚህ አምጣልን፤ ወደዚህ ውሰድልን ሲሏቸው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይላላኩም ነበር።ይህ መላላካቸው ደግሞ በተለይም አሁን ለተሰማሩበት የንግድ ስራ ትልቅ መንገድ እንደከፈተላቸው እሳቸውም በአንደበታቸው ይናገራሉ፡፡

በመሆኑም በ1988 ዓ.ም የጀመሩት መላላክ በተለይም ምግብ ቤቶች ጋር እየሄዱ ምግብ ማምጣት ጥሩ የስራ ፍላጎት አሳደረባቸው፤ በየትኛው ዘርፍ ቢሰማሩም ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ በዛውም አመላከታቸው።በመሆኑም "ምግብ አምጣለን" እያሉ የሚልኳቸው ሰዎች በመበራከታቸው ብልጡ የንግድ ሰው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይሉት አይነት ነገር እግረ መንገዳቸውን ገበያውን ማጥናት የት ምን ማደረግ አለብኝ የሚለውን በምን ብሰማራ ነገን ብሩህ አደርጋለሁ የሚለውን ማየት ጀመሩ፤ እውነትም ይህ ልፋታቸውና ድካማቸው ብሎም

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ብልህነታቸው ታክሎበት የዛሬውን ጠንክርን እንዲፈጥሩ ምክንያት ሆናቸው፡፡

ስራ ወዳዱ የብዙዎች ገመና ከታች የሆኑት አቶ ጠንክር ምን ቢያምራቸው ገንዘብ ማጥፋት ላይ ቁጥብ ናቸው።በዚህም ሊስትሯቸውን ብሎም ሱቅ በደረቴያቸውን እንዲሁም ለሚልኳቸው ሁሉ እየተላኩ አልበላም፤ አልጠጣም፤ አልዘንጠም ብለው ባጠራቀሙት ገንዘብ ምግብ ቤት የመክፈት ፍላጎት አደረባቸው።ፍላጎትን ወደተግባር ለመለወጥ ምንም የማይሳናቸው ግለሰቡም ያጠራቀሙትን 6ሺ ብር በመያዝ የምግብ ቤት ስራን ‹‹ሀ›› ብለው ጀመሩ፡፡

ወትሮም የሰው ፍቅር የስራ ፍላጎት የነበራቸው አቶ ጠንክር "ማሜ ምግብ ቤት" ብለው በከፈቱት ምግብ ቤት ውስጥ እንደ አዲስ ገበያ ፈላጊ እንደ ጀማሪ ነጋዴ አልተቸገሩም፤ ይልቁንም በደህና ቀን ያፈሯቸው ወዳጆቻቸው ለውጣቸውን ሲያዩ እጅግ ተደሰቱ፤ በሌላው ቀን ከሚመገቡበት ምግብ ቤት ንቅል ብለው የእሳቸውን ቤት መቀላቀል ጀመሩ፤ በዚህ ደግሞ ከፍ ያለ የስራ ሞራልና መበረታት ለበለጠ ስኬትም አበቃቸው፡፡

በስድስት ሺ ብር መነሻ ገንዘብ የተጀመረው "ማሜ ምግብ ቤትም" በመጀመሪያው የስራ ቀኑ ብቻ 49 ብር ሰራ ፤ ይህ ለታታሪውና ለስራ ሰው የምግብ ቤት ባለቤት ጥሩ መነሳሳትን ፈጠረ፤ በቀጣዩ ቀን ደግሞ ደንበኞች በጣም በመብዛታቸው ለምሳ የተዘጋጀው ምግብ ገና 6 ሰዓት ላይ አለቀ።እሳቸውና ሁለት ሰራተኞቻቸውም የሚመጡትን ደንበኞች ፍጹም ተደስተው እንዲሄዱ ከፍ ያለ ትጋትን ያሳዩ ነበር።በወቅቱ ምግብ ቤቱ ላይ መጥተው የሚመገቡት ሁሉ በምግቡ ጣዕምና በመስተንግዶው ረክተው ከመሄዳቸውም በላይ በባለቤቱ ስራ ወዳድነትና ለውጥ ፈላጊነት ተደሰቱ።

ይህ ምግብ ቤት ስራው ጠንክሮ የደንበኞቹም እርካታ በተጀመረው መልኩ ቀጥሎ የስድስት ወር የልደት በዓሉን ለማክበር በቃ።በዚህን ጊዜ በጣም የሚገርመውና የባለቤቱን ትጋት የሚያሳየው ደግሞ ምግብ ቤቱ በእሳቸውና ሁለት ሰራተኞቻቸው ቢጀመርም ስድስተኛ ወሩ ላይ 17 ሰራተኞችን ያስተዳድር ነበር።ይህ ሁኔታ ደግሞ ብዙዎችን ያስደነቀ ሆኗል፡፡

አቶ ጠንክር ቴኒ ገንዘብን በቁጠባ መጠቀም ላይ ጽኑ እምነት አላቸው።እያንዳንዱ ገንዘብን ሳንቲም እሳቸው ጋር ሲደርስ ላቅ ያለ ዋጋ አለው።በዋዛ ፈዛዛ የሚባክን አምስት ሳንቲም የለም።ሱስ የለባቸውም በጠቅላላው ገንዘብን የሚያውሉት ነገ ይቀይረኛል ብለው ለሚያስቡት ስራ ብቻ ነው።ይህ ደግሞ በእጅጉ የጠቀማቸው አካሄድ ነው፡፡

አቶ ጠንክር ስራ መስራት ብቻውን ዋጋ እንደሌለውና የሰሩት በአግባቡ መጠቀም በተለይም ቁጠባ ትልቅ ዋጋ ያለውና ከፍ ያለ ቦታ ላይ የሚያደርስ ስለመሆኑ አብዝተው ይመክራሉ።

ተወልደው እዚህ እስከሚደርትሱበት ጊዜ ድረስ የጊዜና የገንዘብ አጠቃቀም የገባቸውና ምንም ዓይነት ብክነት ያላሳዩት አቶ ጠንክር ቴኒ የከፈቱትን ምግብ ቤት በየጊዜው የተለያዩ ተጨማሪ ምግቦችን እያካተቱ ቤቱንም ለእንግዶቻቸው በሚመጥን ሁኔታ እያዘጋጁ ዓመታትን አስቆጠሩ።በእነዚህ ዓመታት እርሳቸው ጥሩ የሚባል ገንዘብን ያገኙበት ከመሆኑም በላይ ለበርካታ ወገኖችም የስራ እድልን በመክፈት የብዙዎችን ጓዳ ሲሞሉ ሰዎች ሰርተው በሚያገኙት ገንዘብ ቤተሰባቸውን መርተው እንዲኖሩም ሲያስችሉ ነው የኖሩት፡፡

ማንም ሰው ትልቅ ሆኖ አልተፈጠረም ትልቅም ትንሽም የሚያደርገው ስራና ስራ ብቻ ነው።ለዚህ ማሳያው ደግሞ የአቶ ጠንክር ቴኒ የሕይወት መንገድ ይመስለኛል።ትላንት



**ስራ መስራት ብቻውን ዋጋ እንደሌለውና የሰሩት በአግባቡ መጠቀም በተለይም ቁጠባ ትልቅ ዋጋ ያለውና ከፍ ያለ ቦታ ላይ የሚያደርስ ስለመሆኑ አብዝተው ይመክራሉ**

ከጋዜጠኞች ጀምሮ የብዙዎችን ጫማ ጎንበስ ብለው ያጸዱ ነበር፤ ያኔም ቢሆን ግን በቻሉት መጠን ባላቸው ነገር ለብዙዎችም የሚደርሱም ነበሩ፤ ዛሬ ደግሞ ሌላ ቀን ነው፤ በትጋትና በጥረታቸው ሕይወታቸውን ስኬታማ ከሚባል ደረጃ ላይ ማስቀመጥ ችለዋል።ይህ ደግሞ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ምሳሌ የሚሆን ነው።አቶ ጠንክር ከዚህም ባሻገር የጠንካራ ሰራተኝነትና የጥረት ውጤትም ናቸው፡፡

የጥንካሬ ተምሳሌት የሆኑት አቶ ጠንክር አሁን አቅሙም ገንዘቡም እንዲሁም የሰውም ተቀባይነት እንዳላቸው አረጋግጠዋል፤ ከዚህ የተነሳም በ2001 ዓ.ም ፊታቸውን ከፍ ወዳለ ነገር ለማዞር ወሰኑ፤ የብዙዎች መዝናኛ እንግዳ መቀበያ ሰርግ ልደት ምርቃት ሌላም ሌላም የደስታ ሁነቶችን ማስተናገጃ የሆነውን "ቶቶት የባህል ምግብ አዳራሽ" እውን አደረጉ፡፡

ይህ የባህል ምግብ አዳራሽም አገርን የመወከል በተለይም የስራ ወዳዱን የጉራጌን ማህበረሰብ የማስተዋወቅ አቅም ያለውን የባህል ምግብ አዳራሽ ላለፉት 14 ዓመታት እየመሩ እዚህ ደርሰዋል፡፡

አቶ ጠንክር የባህል ምግብ ቤት በመክፈታቸው ከ 202 ያላነሱ ወጣቶች ስራ እንዲያገኙ፤ ራሳቸውን እንዲችሉ ቤተሰብ መስርተው አገር እንድትቀጥል እንዲያስችሉም የራሳቸውን ሚና በመወጣት ላይ ናቸው፡፡

አቶ ጠንክር እንደ ብዙዎቹ አሰሪዎች ሰራተኛን ራሳቸው ጋር ዘላለም እንዲቆይ አይፈልጉም፤ አይመክሩምም፤ ከባዶ ተነስተው ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል ማሳያ የሆኑ ሰውም በመሆናቸውም ሰራተኞቻቸው በሚሰሩት ስራ ቤተሰባቸውን ከመምራትና ከማስተዳደር ባሻገር ሰፋ ያለ እቅድን ይዘው ነገን ለማሳመር ብሎም የራሳቸውን ስራ አስበው በዛ መልክ እንዲጓዙ ሁሌም ይመክራሉም።አንዳንዶቹም ይህንንን ህልማቸውን አሳክተውላቸዋል፡፡

አቶ ጠንክር አላማዬ ተሳክቷል፤ በቃኝ ብለው አይቆሙም ሁሌም አዲስ ነገር ያስባሉ።በሌላ በኩል ደግሞ የማገኘው ገንዘብ የእኔና የቤተሰቤ ብቻ ነውም አይሉም፤ ከዛ ይልቅ በተወለዱበት አካባቢ የሚጎድሉ የመሰረተ ልማት ስራዎችን ለመስራት ሁልጊዜም ዝግጁ ናቸው።በዚህም አካባቢያቸው ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር በመቀናጀት መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ ውሃና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን በመዘርጋት ስራ ላይ በግንባር ቀደምትነት ይካፈላሉ።

በሌላ በኩልም የአቅመ ደካሞችን ቤት በመስራት ለወጣቶች የንግድና የፈጠራ ስራ ላይ ድጋፍ በማድረግ ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡም ሰው ናቸው፡፡

የስራ ፈጠራ እንዲሁም የጥንካሬ ተምሳሌት የጥሩ ስብዕና ባለቤት ብሎም ለሌሎች የስራ እድል ፈጣሪ በመሆናቸውም ነሐሴ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በተካሄደው የበጎ ሰው ሽልማት ላይ ቀርበው አሸናፊ ለመሆን ችለዋል፡፡

# ባህልና ቱሪዝም

# መስቀል ደመራ- የቱሪዝም ዘርፉ አነቃቂ ሃብት

ዳግም ከበደ



የያዝነው የመስከረም ወር ለቱሪዝም መስህብነት የሚውሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት በብዛት የሚስተናገዱበት ነው። ክብረ በዓላቱ የሚጀምሩት ኢትዮጵያን ከመላው ዓለም ልዩ በሚያደርገው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደምቆ ከሚውልበት መስከረም አንድ የአዲስ አመት "እንቁ ጣጣሽ" በዓል ነው፡፡

የወላይታ ብሔረሰብ ዘመን መለወጫ /ጊፋታ/፣ የሀዲያ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ ያሆዴ፣ የጎፋና ጋሞ የመስቀል በዓላት፣ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል እንዲሁም በኦሮሞ ብሔር ዘንድ በድምቀት የሚከበረው የኢሬቻ በዓል በእዚሁ ወር የሚስተናገዱ በዓላት ናቸው፡፡

ወሩ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ በዓለም ቅርስነት በተመዘገቡ እና በቀጣይ ሊመዘገቡ በሚችሉ ልዩ ልዩ የማይዳሰሱ ክብረ በዓላት ይደምቃል፡፡ ይህን ተከትሎም ታላላቅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ጉዞዎች ይደረጋሉ፡፡ በነዚህ ወቅቶች የአገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች ወደ መላ ኢትዮጵያ በብዛት ይንቀሳቀሳሉ።

ይህ ወር የዓለም ቱሪዝም ቀን በመላ ዓለም የሚከበርበትም ነው፡፡ በዓሉ ዘንድሮ በዓለም ለ43ኛ ጊዜ በኢትዮጵያም ደግሞ ለ35ኛ ጊዜ እየተከበረ ይገኛል፡፡ ቀኑ በኢትዮጵያ እንደ አገር በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግስት ትናንት መከበር የጀመረ ሲሆን፣ በዛሬው እለት /መስከረም 15/ የበዓሉ ማጠቃለያ ይደረጋል፡፡

የዓለም ቱሪዝም ቀን "አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም" በሚል መሪ ሃሳብ እየተከበረ የሚገኝ ሲሆን፣ በዋናነት በቱሪዝም ዘርፉ የተከናወኑ ዘርፈ-ብዙ ስኬቶች የሚዘከሩበት መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በበዓል አካባበሩ ወቅትም በተለያዩ የመስህብ ስፍራዎች ጉዞዎች ይደረጋሉ፡፡

ይህ ሁነት በማይዳሰስ የዓለም ቅርስነት የተመዘገበውን "የመስቀል ደመራ" ክብረ በዓልና ሌሎች በዓላቱን ከምንጊዜውም በተሻለ የዓለም ትኩረትን እንዲስቡና የቱሪስት ፍሰቱ ይበልጥ እንዲጨምር ሊያደርጉ በሚያስችሉ መልኮች ማክበር መቻል የመስህብ ሃብቶቹንም ለማበልፀግ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በየዓመቱ በመስከረም ወር የሚከበረው ይህ ቀን የኢትዮጵያውያን የዘመን መለወጫ ወር ሊባል በሚችለው መስከረም ወር እና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ዘንድ በየአመቱ በድምቀት በሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል ሰሞን መዋሉ ለበአላቱ ድርብ ድምቀትን ያጎናጽፋልና በቀጣይም በድምቀት ቢከበር ፋይዳው ከፍተኛ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በዚህ በመስከረም ወር ለዘመናት የዓለምን ቀልብ በመሳብና በሃይማኖታዊና ባህላዊ ስርዓቱ በእጅጉ የሚታወቀው "የመስቀል ደመራ" በዓል ነገና ተነገ ወዲያ በድምቀት ይከበራል። በነገው እለት በመስቀል አደባባይ የደመራ በዓል በልዩ ደማቅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስነስርአት የሚከበር ሲሆን፣ በቀጣዩ ቀንም የመስቀል በዓል ቀጥሎ ይውላል።

የመስቀል ደመራ በዓል በወሩ በመላው ዓለም በሚመጡ ቱሪስቶችና ኢትዮጵያውያን በጉጉት ይጠበቃል። የመስቀል ደመራ በዓል በዩኒስኮ በማይደሰስ ቅርስነት መመዝገቡም ይታወቃል፡፡ ይህ ምቹ ሁኔታ ደግሞ የአገሪቱ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር ዓይነተኛ ምክንያት ይሆናል። ለመሆኑ ይህ በዓል ምን አይነት ይዘት አለው? በምን መልኩስ ይከበራል? በኢትዮጵያ ቱሪዝም ላይስ ምን ተፅእኖ ያሳድራል? የዝግጅት ክፍላችን የባህልና ቱሪዝም አምድም በዋናነት ነገ በመስቀል አደባባይ የሚከበረውን ይህን የመስቀል ደመራ በዓልና በማግስቱም በየቤቱ የሚቀጥለውን የዚህን በዓል ስነስርዓት እንደሚከተለው አሰናድቶታል።

## መስቀል ደመራ

መስከረም ለእኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ ፀጋና በርካታ በረከትን ይዞልን ይመጣል። ሁሌም የያዝነው ዓመት ተጠናቆ አዲሱን ስንቀበል በወጋገን ፈክተን በልምላሜ ተከበን በአደይ አበባ አጊጠን ነው። እኛ የራሳችን የዘመን መቁጠሪያ፣ የራሳችን ፊደልና ከተፈጥሮ ጋር የምንግባባበት ልዩ ቀመር ያለን ህዝቦች ነን። ለዚያ ነው ጉሙና ጨለማው ሲገፍ አበቦች በፍካት ሲፈነድቁ በራችንን ከፍተን በልዩ ተስፋ ተውበን ዘመኑን የምንቀበለው።

መስከረም ሲጠባ አሮጌውን ዓመት ብቻ አንሸኝም፤ አዲሱን አመት ብቻውንም አንቀበልም። ልዩ ልዩ በዓላትን እናከብራለን፤ ለቀጣዩ ወራት እቅድ አውጥተን የሕይወት ስኬት ለማስመዝገብ የምንሰናዳበት ጭምር እንጂ።

አዲስ ዓመት ሁሌም ይናፈቃል። ሁሉም የአገሬ ሰው በዚህ ጊዜ በደስታ ይቅበጠበጣል። ከላዩ ላይ እርጅና የሚለውን ስያሜ ገፍፎ ደምቆና አምሮ ይታያል። በሸኘው ዓመት ያገኘውን ድል በአዲሱ ደርቦ ደራርቦ ስኬታማ ለመሆን ያቅዳል። ማንፀባረቁ የፊት ገፅታው ላይ ሲገለጥ፣ ማማሩ ደግሞ ከባህላዊ እሴቱ በተቀዳው ማራኪ አልባሳት ማጌጡ ላይ ይታያል። በአጠቃላይ አዲስ ዓመት ሁሌም አዲስ ሁሌም ፍካትን የሚሻበትና "አሃዱ" ብሎ ዳግም የሚነሳበት ወቅት ነው።

መስከረም ለእኛ ብቻ አይጠባም። ወሩን ጠብቀው ውብ ባህላችንን፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን እንዲሁም ልዩ ልዩ መገለጫዎቻችንን ለመጎብኘት ከተለያዩ የዓለም ክፍል አገራት ወደ ውቢቷ አገራችን ለሚጎርፉ አያሌ የውጭ ዜጎች መስከረም ይጠባል፤ ይህን ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ ይተማሉና፡፡ እኛ ልዩና ውብ ባህል፣ ማንነት ያለን ህዝቦች ነን። በዚህ ምክንያት ደግሞ ብዙዎች ያሉንን እሴቶች ለማየት ይናፍቃሉ። እኛም እንግዳን ተቀብለን "እሽሞንሙነንና" ዳግም ደጃችንን እንዲናፍቅ አድርገን መሸኘት የምንችል ኢትዮጵያውያኖች ነን።

ለምሳሌ ነገ ደመራ ነው። መላው ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የመስቀል በዓልን ለማክበር "በመስቀል አደባባይ" ተገኝተው ደመራ ደምረው በሃይማኖታዊ ስርዓት ደምቀው የሚውሉበት እለት ነው። ይሄ ክንውን በዓመት አንዴ የሚመጣ ከመሆኑ አንፃር በምእመናኑ ብቻ ሳይሆን ከመላው ዓለም ለሚጎርፉ ጎብኚዎች፣ የሌላ እምነት ተከታዮች በሆኑትና ተባብሮና ተቻችሎ የመኖር እሴት በገባቸው ኢትዮጵያውያን ጭምር የሚናፈቅ ነው።

መስከረም አንድ ሲል "አበባ አየሽ ወይ" ብለን ቢጫውን የተስፋ ምልክት አደይ አበባን ይዘን በደስታ እንደምንቀበለው ሁሉ በመስከረም 16 እና 17 ደግሞ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች "የመስቀሉን ከጠፋበት በንግስት እሌኒ አማካኝነት መገኘትን» ምክንያት በማድረግ ሌላ ብስራት ሌላ ደማቅ በዓል ኢትዮጵያ እንድታከብር ያደርጋሉ።

በዚህ በዓል ውስጥ አንድነት፣ ፍቅር፣ ባህል፣ ማንነትና ውብ ስነስርዓት በጎዳናና በሰፋፊ አደባባዮች ላይ ይታያል። ይሄኔ ዓለም ፊቱን ወደ እኛ ያዞራል። ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንት ጎልማሶች ሴት ወንዱ ሳይቀር እምነቱ በሚፈቅደው ስርዓት አምሮና ተውቦ ከነብሱ ምግብ በተጨማሪ እግረ መንገዱን ባህሉንና ታሪኩን ያስተዋውቃል። ጎብኚዎች ካሜራዎቻቸውን ደቅነው፣ አይኖቻቸውን አጉልተውና ነብስያቸውን በሙሉ በመስቀል አደባባይ በሚደረገው "ሃይማኖታዊ ትርኢት" ላይ ጥለው እምነት፣ ስርዓት፣ ባህል፣ ውበት፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ይደመሙበታል። ምን ይሄ ብቻ በባህላዊ ልብሶቻችን ደምቀውና አጊጠው በጎዳናዎች ላይ ሽር ብትን ይላሉ።

## በመስቀል ደመራ ጊዜ

"መስቀል ከጎለጎታ እስከ ግሸን ደብረ ከርቤ" በሚለው መፅሃፍ ላይ ደመራ ሲሆን (በመስቀል በዓል) እረኞችና ወጣቶች የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎች ይጫወታሉ፤ እናቶችና አባቶችም በተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በቆየው የኢትዮጵያውያን ሥርዓተ ባህል መሠረተ ተራው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ ነገሥታት አዲስ አዋጆችን የሚያውጁ በየቤቱና በየአካባቢው ተበታትኖ የከረመውን ሠራዊታቸውን ክተት ብለው የአደባባይ ላይ ትርኢት የሚያሳዩበት በዓል ጭምር መሆኑን ይገልፃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለመኳንቶቻቸው፣ ለካህናትና ለታላላቅ እንግዶች ግብር የሚያበሉበት፣ ከእኒህ አካላት ጋራ በአገርና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚወያዩበት ዕለትም ነው። ሕዝቡም በየጎጡና በየሰፈሩ በነቂስ በመውጣት የደመራ በዓሉን በድምቀት ካከበረ በኋላ በኅብረት እየተመገበና እየጠጣ ስላለፈው ክረምትና ስለመጪው መኸር ጉዳይ የሚጨዋወትበት ልዩ አጋጣሚ ነው፡፡ በተለይ የአገር ሽማግሌዎች ሰብሰብ ብለው የሚወያዩበት ዕለት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የመስቀል በዓል ልዩ የሚያደርገው ሌላው ገጽታው ሰዎች በክረምት ምክንያት ተለያይተው ከከረሙ በኋላ የሚገናኙበት፣ እሸት የሚደርስበትና የሚቀመስበት ወቅት መሆኑም ጭምር ነው፡፡ ጊዜው የዘርና የአረም ሥራ የሚያበቃበት፣ በአንጻሩ እህሉ ለእሸት፣ ለአጨዳ የማይደርስበት፣ ገበሬው ከአድካሚው የክረምት ሥራ ተላቆ አንጻራዊ ዕረፍት የሚያገኝበት በመሆኑ ተለያይቶ የከረመው ወዳጅ ዘመድ ለመጨዋወትና ለመገናኘት ያመቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን የመስቀልን በዓል የሚያከብሩት ብቻቸውን አይደለም፤ ዕፅዋቱም፣ እንስሳቱም ምድሪቱም ሰማዩም ከሰው ጋራ ተስማምተው ተዋሕደው ነው የሚያከብሩት ማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ መስቀል የጠለቀ ዕውቀት እንዳለው የሚያሳዩ የተለያዩ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ ገበሬው ሌላው አካሉ ጥቁር /ዳልቻ/ ኾኖ ግንባሩ ነጭ ያለበት በሬውን መስቀል፣ በተመሳሳይ ላሙን መስቀሌ እያለ ነው ይጠራቸዋል፡፡ ይህም ምሳሌያዊ ነው፡፡ ይኸውም አንደኛው ምክንያት የሰው ልጅ ለ5500 ዓመታት በጨለማ ከቆየ በኋላ እውነተኛ ብርሃን ያገኘው ከመስቀል በኋላ መሆኑን ለማሳየት ሲሆን በሌላ አባባል መስቀል የብርሃን ተምሳሌት መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ በትግራይ ሰዎች አደይ አበባን ገልገለ መስቀል /የመስቀል አጃቢ/ ብለው የሚጠሩትም ለዚሁ ይመስላል፡፡ የመስቀል ወፍን ጉዳይ ሳንረሳ ማለት ነው፡፡

## ሃይማኖታዊ ስርዓት

ነገ የመስቀል ደመራ በዓል በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበርበት ቀን ነው። ሁሉም በየመንደሩ ባለ ክፍት ቦታ ላይ ነገ ከጠዋት አንስቶ ደመራ ያቆማል፤ ደመራው በዓደይ አበባ ያጌጠ በችቦና በደረቅ እንጨት፣ በቄጤማና በኢትዮጵያ ባንዲራ ይዋባል። ምን ይሄ ብቻ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ" ቤተክርስቲያንና ምእመናን አብያተ ክርስቲያናት በሚያዘጋጇቸው ደመራዎች ወይም "በመስቀል አደባባይ" በሚዘጋጅ ታላቅ ደመራ በአንድነት ተደምረው አምላካቸውን "ለኢትዮጵያ ሰላሙን" እንዲያመጣላት፣ አንድነቷን እንዲመልስላት የሚለማመኑበትና ፀሎት የሚያደርጉበት ቀን ነው።

ከሁሉም ደብር የሚመጡ ዘማሪያን፣ የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም ምእመናን በየ"መስቀል አደባባዩ" እጅግ ግዙፍ ደመራ ይዘጋጃሉ። ደመራው በሃይማኖት መሪዎች ተባርኮ፣ ዝማሬ ተደርጎ፣ ቀልብን የሚስብ እንደ ያሬዳዊ ዜማና ወረብ በመሳሰሉ ስነስርዓቶች ደምቆ "ደመራውን" በእሳት የማያያዝ ስነስርዓት ይካሄዳል። ይሄንም ሁሉም ጧፉን እያበራ "እልልታው" እያሰማ አስደማሚ ትእይንት ይካሄዳል።

ሃይማኖታዊ ስርዓቱን በደንብ የማያውቁት "ቱሪስቶች" በመደነቅ እጃቸውን አፋቸው ላይ ጭነው ትእይንቱን ይታደማሉ። በተለይ እንደ አዲስ አበባው መስቀል አደባባይ ባሉ ስፍራዎች የሚከበረው የደመራ በዓል ቀኑ እየመሸ፣ ደመራው ሲለኮስ፣ ጧፉ ከዳር እስከ ዳር ሲቀጣጠል ለተመለከተ ከውጭ ለመጡት ብቻ ሳይሆን ሁሌም በየአመቱ በስፍራው ተገኝተው ስነስርአቱን የሚታደሙትን ጭምር ሁሌም ያስገርማል፡፡ ምን ይህ ብቻ፤ በቴሌቪዥን መስኮት በሚከታተሉት ላይም ጭምር ልዩ ስሜትን ያጭራል፡፡

## መስቀል (ደመራ) የዓለም ቅርስ

ከዓመታት በፊት የኢትዮጵያው "የመስቀል ደመራ ክብረ በዓል" በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል፡፡ ዩኔስኮ የመስቀል ክብረ በዓልን (Commemoration feast of the finding of the True Holy Cross of Christ) በዓለም ቅርስነት መመዝገቡን ይፋ ያደረገው፣ በማይዳሰሱ (መንፈሳዊ) ባህላዊ ቅርሶች ጥበቃና ክብካቤ ላይ የሚሠራው ኮሚቴ ስምንተኛውን ጉባኤ ባካሄደባት የአዘርባጃኗ ባኩ ከተማ ነው፡፡

የመስቀል ክብረ በዓል የኢትዮጵያን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊቶችን የያዘ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ መምጣቱና በአገሪቱ ማኅበራዊ አንድነትንና የእርስ በርስ ትስስርን፣ ብዝኃነትን የሚያንጸባርቅ፣ በበርካታ ብሔረሰቦች ባህሎች መካከል ትስስርን የፈጠረ በመሆኑ ዓለም አቀፍ መስፈርቱን እንዲያሟላ አድርጎታል፡፡ በዚህ መነሻ በዚህ ወር ቱሪስቶች ከየአቅጣጫው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባትና ስነስርዓቱን በቀጥታ ለመታደም ይፈልጋሉ።

ባለፉት አመታት አንዴ በኮረና ወረርሽኝ ከዚያም በጸጥታ ችግር ሳቢያ የመስቀል በዓል እንደ ሁልጊዜውም በመላ አገሪቱ በደማቅ ስነ ስርዓት አለመከበሩ ይታወሳል። ዘንድሮ በዓሉ ከቀደሙት ዓመታት በተሻለ ድምቀት እንደሚከበር ይጠበቃል።

ነገ በሚከበረው የ"መስቀል ደመራ" በዓል ከ9ሰዓት ጀምሮ የበዓሉ ታዳሚያን የሃይማኖት አባቶች፣ ምእመናን፣ ስነስርዓቱን ለመመልከት ብዙ ሺ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው የመጡ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጎብኚዎች እንዲሁም የመንግስትና የግል ተቋማት ተወካዮች ደመራው ወደሚከበርበት "መስቀል አደባባይ" ይተማሉ። ደመራውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስነ ስርአት መሰረት በድምቀት ይከበራል፤ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ተስፋ የበለጠ ሊያደምቅ ይለኮሳል።

ይህ ሃይማኖታዊ ፋይዳ ብቻ ሳይሆን ለቱሪዝም ዘርፉም አነቃቂ የሆነ በዓል በድምቅትና በሰላም እንዲከበር እየተመኘን እንሰናበታለን፡፡ ሰላም!

# ሳምንቱን በታሪክ

# ብላቴ ጌታ ህሩይ ወልደሥላሴ

ተገኝ ብሩ

“ህሩይ” በግዕዝ ምርጥ ወይም የተመረጠ ማለት ነው። መጀመሪያ” ህሩይ” የሚል መጠሪያ የእርሳቸው ስያሜ አልነበረም። አባታቸው ወልደ ስላሴ ለሚወዱት ልጃቸው ያወጡላቸው ቀዳሚው ስም ገብረመስቀል ነው። በአባታቸው የወጣላቸው ገብረመስቀል የተሰኘ ስማቸውን የለወጡት አንድ መምህር ናቸው። የብላታ ህሩይ ብሩህ አዕምሮና በስነ ምግባር የላቀ መሆኑን የተመለከቱት መምህር ገብረመስቀል የሚለው ስም እስከመጨረሻው ድረስ የታወቁበትና ገናና የሆኑበት ስማቸው “ህሩይ” ብለው ለወጡት።

እኚህ አገር ወዳድ ድንቅ ኢትዮጵያዊ፣ የታሪክ ተመራማሪ፣ ደራሲ፣ ዲፕሎማትና የሃይማኖት አባት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተደጋግመው የሚነሱና ባበረከቱት ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ ተጠቃሽ ናቸው። እኚህ የአገር ባለውለታ ብላታ ጌታ ህሩይ ወልደስላሴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በዚህ ሳምንት መስከረም 9 ቀን 1931 ነበር። በዛሬው የሳምንቱን በታሪክ አምዳችንም እኚህን የአገር ባለውለታ ልናነሳ ወደድን።

በሰሜን ሸዋ በመርሐ ቤቴ አውራጃ በታች ቤት ወረዳ ረመሸት ቀበሌ ደን አቦ ገዳም ከአባታቸው ወልደሥላሴ እና ከእናታቸው ወይዘሮ ወለተማሪያም በ1871 ዓ.ም የተወለዱት ብላታ ጌታ ህሩይ በሕይወት ዘመናቸው በተለያየ መስክ አገራቸውን በፅናት አገልግለዋል፤ ለህዝባቸው ነፃነትና ስልጣኔ ታግለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመሆን አገራቸውን ያገለገሉት ህሩይ ወልደሥላሴ መሪ ብቻ ሳይሆኑ እውቅ ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪና ጎበዝ ዲፕሎማት ነበሩ። ወደ ቀለም ትምህርት ቤት የገቡት በአባታቸው ወልደስላሴ ምክንያት ነው። አባታቸው በብዙዎች ባለመማራቸው ትችት ይደርስባቸው ስለነበር ይህ ቁጭታቸውን ልጃቸውን በማስተማር ለመወጣት ቆረጡ።ልጃቸው ህሩይ ለትምህርት ሲደርስ መጀመሪያ ያደረጉት ወደ ቀለም ትምህርት ቤት ማስገባትና ፊደል መቁጠር እንዲጀምር መርዳት ነበር፡፡

አባት ወልደሥላሴ ልጃቸው ህሩይን ገናቦ ገዳም በሚገኝ ትምህርት ቤት አስገብተው ትምህርት እንዲጀምር አደረጉ። በዚያም ፊደል ቆጥረው ንባብ ለይተው ከፍተኛው የቤተክርስቲያን ትምህርት መከ ታተል እንዲችሉ ከመረሀ ቤቴ እስከ ስላሴ ከዚያም እስከ ሸሬ መድኃኒዓለም ድረስ እየወሰዷቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ብርቱ ክትትልና ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር።

ታታሪና የቀለም ቀንድ የነበሩት ብላታ ጌታ ህሩይ፤ በዜማ ትምህርት እስከ መምህርነት ደረጃም ደረሱ። ቀጥለውም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት እንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የመፅሐፍን ትርጓሜና ልዩ ልዩ የሃይማኖት ትምህርቶችን በዘመኑ ከነበሩት የደብሩ ሊቃውንት ተምረዋል። ትምህርቱንም በከፍተኛ ደረጃ እና ውጤት አጠናቀቁ።

በወቅቱ የራጉኤል የደብር አለቃና የአፄ ምኒልክ የፅሕፈት ሚኒስትር የነበሩት ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ ወልደአረጋይ ከደብሩ ሊቃውንት ስለ ብላታ ህሩይ ዝና በተደጋጋሚ ሰምተው ወደሳቸው እንዲቀርቡ አደረጉ። ሚኒስትሩም ህሩይ ያላቸውን ድንቅ ችሎታና ታታሪነት ተመልክተው ከቤተክርስቲያን ሊቃውንቱ ጋር ንጉሱ ዘንድ ቀርበው እንዲሸለሙም አድርገዋል፡፡

አፄ ምኒልክም በወቅቱ ለሽልማት ከቀረቡት በእድሜ ከሁሉም አነስተኛ የነበሩት ብላታ ህሩይ ወልደሥላሴን ተመልክተው “እንደው ይሄ ልጅ ትንሽና ገና ብዙ ስራ የሚጠበቅበት ሆኖ ሳለ ለሽልማት መቅረቡ እንዴት ነው” ብለው ሲጠይቁ የፅሕፈት ሚኒስትር የነበሩት ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ ወልዳረጋይ “ጃንሆይ ልጁ እድሜው ነው እንጂ እውቀቱ ትልቅና አስገራሚ ነው፡፡” በማለት የነበራቸውን ብሩህ አዕምሮና ችሎታ መስክረውላቸዋል።

ከሽልማቱ በኋላ ህሩይ በተለይ በቤተ መንግስትና በቤተክህነት ስማቸው ተደጋግሞ ይጠራ ጀመር። ቀስ በቀስም በሁሉም ዘንድ መታወቅና ተወዳጅነት ማትረፍም ቻሉ። በተለይ በነበራቸው የስነ ፅሁፍ ችሎታ፣ የታሪክና የሃይማኖት እውቀት በብዙዎች ዘንድ አንቱታን አተረፉ፡፡

ወደ ጋብቻ የገቡትም በወጣትነት እድሜያቸው ነበር። ወይዘሮ ህመረ እሸቴን በቤተክርስቲያን ስርዓት አግብተው አራት ሴቶችና ሁለት ወንድ ልጆችን ማፍራትም ችለዋል። በኋላም በእንግሊዙ ንጉስ ጆርጅ 5ኛ የንግስና ስርዓት ላይ ለመገኘት ከኢትዮጵያ ከተወከሉ ሉዑኮች ጋር ወደ እንግሊዝ አቅንተው እግረ መንገዳቸውም ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ፣ ፓሪስ፣ ሮም፣ ስክንድሪያና ካይሮ በመዞር ስለ ስልጣኔና አዳዲስ ሀሳቦችን መቅሰም ቻሉ። በዚህም በዘመኑ በአገራችን ከነበሩ ሰዎች የተለየ ዘመናዊ አመለካከት እንዲላበሱ አድረጓቸዋል።

ከተመለሱም በኋላ የመጀመሪያው የአማርኛ መፅሀፍ ትርጉም ከአለቃ ታዬ ጋር ለማዘጋጀትም በቅተዋል። ከዚያም በነበራቸው የተለየ ተስጥኦና የዳበረ ልምድ ህዝባቸው ይጠቅሙ ዘንድ የአዲስ አበባ አስተዳደር ዳይሬክተር ሆነው ተሾሙ።የከተማዋ ፕላንና ግብር እንዲሁም ልዩ ልዩ የአስተዳደር ስርዓቶችን በአዲስ መልክ በማስጀመር ታላቅ ውለታን የሰሩ ናቸው፡፡

በወቅቱ የከተማ አስተዳደር ስርዓትን “ማዘጋጃ ቤት” ብለው በመሰየም አዲስ አሰራር መዘርጋት የጀመሩት እሳቸው ናቸው። በዚህም የአስተዳደር ስርዓቱን ምቹ እንዲሆን አድርገዋል።

በ1914 ዓ.ም በኢትዮጵያያ የውጭ አገር ዜጎች ጉዳይን በሚመለከት ፍርድ ቤት ብላታ ተብለው ማዕረግ ተሰጣቸው ዳኛ ሆኑ።ከዚያም የኢትዮጵያ መንግስት የቅርብ አማካሪ በመሆንም አገልግለዋል። ከአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ጋር በመሆንም በድጋሚ አውሮፓን ጎብኝተዋል። በ1919 ዓ.ም ደግሞ ብላቴን ጌታ ተብለው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዳይሬክተር ሆነው አገልግለዋል። ከ1922 ጀምሮ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን አገራቸውን ከውጭው ዓለም ጋር በማገናኘትና የአገሪቱን ጥቅም እንዲከበር በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

በተለይም በተለያዩ የአውሮፓ አገራት ለጉብኝት ሲሄዱ ያዩትን አዲስና ለአገር ጠቃሚ ብለው ያሰቡትን ነገር በመቅሰም ወደ አገር ቤት ሲመለሱ እንዲተገበር የሚተጉና ለህዝባቸው ስልጣኔ እጅግ ጉጉም ነበሩ። የኢትዮጵያን ቀይ መስቀል ማህበር በማቋቋምና የመጀመሪያው መሪ በመሆንም አገልግለዋል። በተለይም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ለአገራቸው ይዋደቁ ለነበሩ ጀግኖች የህክምና አገልግሎት በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦም አበርክቷል፡፡

ክቡር ብላቴ ጌታ ህሩይ ወልደሥላሴ በሄዱበት አገር ያገኟቸውን መፅሃፍት ይዘው ወደ አገር በመመለስ የማንበብና የሚውቁትን ነገር ለሌሎች የማድረስ መልካም ልምድም ነበራቸው። ይህም እጅጉን በጠለቀ የማንበብ ፍቅራቸው የበዛ እውቀትን መሸመት አስችሏቸዋል። የተለያዩ ስራ ሀላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሰሩ በነፃነት አዳዲስ አሰራሮችና የስራ ሂደቶች እንዲከተሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ያስቻላቸውም ይህ ነው።

ብላታ ጌታ ህሩይ በተለይም በማህበራዊ ጉዳይ ላይ በሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ በማህበረሰቡ ዘንድ እጅጉን ይወደዱም ነበር። ቤተሰባቸውን በስርዓትና በቤተሰባዊ ፍቅር በመምራት ልጆቻቸው አገራቸውን የሚጠቅሙ እንዲሆኑ በብርቱ ይመክሩ ነበር።

እኚህ ታላቅ የአገር ባለውለታ ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ከንጉስ አፄ ኃይለሥላሴ ጋር በመሆን በስደት ወደ እንግሊዝ አገር ሄዱ። እዚያም ኢትዮጵያ በወራሪዋ ኢጣሊያ ግፍና መከራ እየደረሰባት መሆኑንና የተለያዩ የዓለም አገራት ከኢትዮጵያ ጎን ሆነው ወረራውን እንዲያወግዙ ለማድረግ ብዙ ጥረዋል። እኚህ ኢትዮጵያን በከፍተኛ ባለስልጣንነት ያገለገሉት የአገር ባለውለታው ሰው ህሩይ ወልደ ስላሴ በአገሪቱ የስነ ፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ባበረከትዋቸው ዘርፈ ብዙ የስነ ፅሁፍ ስራዎችም ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው። ከ21 ያላነሱ ልዩ ልዩ መፅሐፍት አዘጋጅተው አሳትመዋል፡፡

በተለይ በብዙዎች ዘንድ የሚጠቀሱ በርካታ ስራዎችን ያበረከቱ ሲሆን ከነዚህም መሀከል፡- ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ ዓድዋ ዘመቻ(ታሪክ)፣ ኢትዮጵያና መተማ (ታሪክ፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ (ታሪክ)፣ ደስታና ክብር(ታሪክ)፣ የሕይወት ታሪክ (ትምህርት)፣ ዋዜማ (ታሪክ)፣ ማኅደረ ብርሃን ሀገረ ጃፓን(ታሪክ)፣ በዕድሜ መሰንበት ሁሉን ለማየት(ታሪክ)፣ መጽሐፈ ቅኔ (ግጥምና ቅኔ)፣ ወዳጄ ልቤ(ልብወለድ)፣ የልብ ሐሳብ(ልብ ወለድ) አዲስ አለም(ልብ ወለድ)፣ጎሐ ጽባሕ(መልክ፣ ገድልና፣ ነገረ መለኮት)፣ ጥሩ ምንጭ(መልክ፥ ገድልና፣ነገረ፣ መለኮት)፣ ስኳርና ወተት( ተረቶችና ቀልዶች)፣ ለልጅ ምክር ላባት መታሰቢያ (ትምህርት)፣ ተጠቃሾቹ ናቸው።

በመጨረሻም ብዙ የደከሙላት አገራቸው በወራሪው ኢጣሊያ እንደተያዘች እዚያ በስደት በቆዩባት እንግሊዝ መስከረም 9 ቀን 1931 ዓ.ም ሕይወታቸው አለፏል።

በቀብር ስነ ስርዓቱ ላይ የተገኙት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በወቅቱ ስለ ብላታ ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ እንዲህ ብለው ነበር።

“አሁን የአዳምን ልጆች ወግ ሲቀበል የምታዩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ በአገራችን ሥርዓት በመልካም አያያዝ ያደገ ከኢትዮጵያም ከፍ ካሉት ሊቃውንት የሚቆጠር ነው። ብልሃቱንና ትጋቱንም ለመልካም ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ስላደረጋቸው በመንግሥታችን ሥራ ለመመረጥና ወደ ታላቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ለመድረስ በቃ። በየጊዜው የጻፋቸው ከፍተኛ ባህሪውን የሚገልጹ መጻሕፍት፤ ይልቁንም በቤተ ክህነትና በታሪክ እውቀት በዓለም ሊቃውንት ዘንድ የታወቀና የተከበረ አደረጉት። ለምታውቁት ሰው ከታሪኩ ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የሚያስፈልግ አልመሰለኝም።

በአጭሩ ከጠባዩ ትልቅነት የሚሰማኝን ለመናገር ሳስብ ጊዜውን ሁሉ ቁም ነገር በመሥራት ማሳለፉ፤ ከራሱ ይልቅ የተቸገሩትን ለመርዳት መጣሩ፤ እውነትን፣ ፍርድንም ማክበሩና በአገር ፍቅር መቃጠሉ ትዝ ይሉኛል።

አገልጋዬና ወዳጄ ኅሩይ! በተቻለህ ስለአገርህ ሥራህን በሚገባ ፈጽመህ በምትሰናበትበት ጊዜ ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይናገራሉ። በክፉ አድራጊዎች የሚገፋ የዓለምን ፀጥታ የሚያናውጥ ነፋስ ምንም ቢያንገላታህና በታላቅ ፈተና ላይ ቢጥልህም ሊያሸንፍ አልቻለም። ታላቅና ቸር በሆነው ጌታ በተመደበው ሕግ ግን መታዘዝ ግድ ሆነብህ። ይህም ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን ዕድል ነው። አንተም እስከ መጨረሻ ከታገልክ በኋላ ዛሬ ደከመህ፣ አንቀላፋህም። በሥጋ ብትለየንም ስምህና ሥራህ በመካከላችን ይኖራሉ።

ኅሩይ! እግዚአብሔር ሲያስበን አጥንቶችህና መንፈስህ የሚሰፍሩበትን ቦታ እስኪያዩና ከአባቶችህ እስኪቀላቀሉ ድረስ በእንግድነት በመጣህበት በዚህ ሥፍራ በሰላም ዕረፍ።”

ምንም እንኳን ለአገራቸው ነፃነት ሲሟገቱ ያረፉት ብላታ ጌታ ህሩይ በእንግሊዝ አገር ስርዓተ ቀብራቸው ቢፈጸምም ከ9 ዓመት በኋላ አፅማቸው ወደ ኢትዮጵያ በንጉሱ አማካኝነት እንዲመጣ ተደርጎ በቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን መስከረም 11 ቀን 1940 ዓ.ም በድጋሚ በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል።ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለአገራቸው እድገትና መሻሻል የራሳቸውን አሻራ ጥለው ያለፉ ታላቅ ምሁር ስለነበሩ በትውልድ ዘንድ ለዘለዓለም ሲታወሱ ይኖራሉ።ለስማቸው ማስታወሻ እንዲሆንም መኖሪያ ቤታቸው የሳይንስ አካዳሚ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡





ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## አበበ ተካ

**አቤል ገ/ኪዳን**

በአሁኑ ወቅት በየትኛው የምሽት ክበብ ጎራ የሚል ሰው የእሱን ሙዚቃ ወጣት ድምጻውያን ሲያዜሙት ይሰማል፡፡ አሁን የተስፋፋው የተለያዩ ሙዚቃዎችን እየቀነጨቡ በአዲስ መልክ መጫወት ላይም ከማይቀሩት ሙዚቃዎች መካከል ዋነኛው የእሱ ሙዚቃ ነው፡፡ ልዩ በሆነ አዘፋፈኑ እና ነፍስ ባላቸው ሙዚቃዎቹ እናውቀዋለን፡፡ አበበ ተካ። በዛሬው የዝነኞች ገፅ አምዳችን በተለያዩ ጊዜያት ስለ እሱ ከተሰሩ ዘገባዎች መርጠን ልናስታውሰው ወደድን፡፡

ትውልድና እድገቱ ጎንደር ከተማ ውስጥ ነው። ከልጅነቱ ነው ከሙዚቃ ጋር በፍቅር የወደቀው፡፡ በልጅነቱ የህንድ ፊልሞችን እያየ በፊልሙ ላይ ያሉ ሙዚቃዎችን እያጠና ሲያዜም ጓደኞቹ ዙሪያውን ከብበው ያዳምጡት ነበር፡፡ ገና የ10 ዓመት ልጅ እያለም በቀድሞው የከፍተኛ ኪነት ውስጥ አባል ሆኖ ሙዚቃ ይጫወት ነበር፡፡ ‹‹የ10 ዓመት ልጅ ሆኜ ነው ሙዚቃን ከታላላቅ አርቲስቶች ጋር የጀመርኩት። ወገራ አውራጃ ዳባት ከተማ የሚባል አባቴ ለስራ ከጎንደር ተዛውረው ወደዛ ሲሄዱ እኔን ነበር ይዘው የሄዱት፡፡ በዚያ ጊዜ ነው ሙዚቃን መስራት የጀመርኩት›› ይላል፡፡ ገና በ12 ዓመት እድሜው

**ሰፊው ህዝብ በሙሉ ያስከው በሀገር ተነሳ በአንድነት እንድንተባበር**

የሚለውን የራሱን ድርሰት ሰርቶ ለህዝብ አቅርቦ የድምጽ ብቃት ብቻ ሳይሆን የደራሲነት ክህሎት ባለቤትነቱንም አረጋግጧል፡፡ ከዚያም በኋላ በ1978 ዓ.ም በኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ውስጥ በ603ኛ ኮር የኪነት ቡድን ውስጥ በመቀላቀል ሙዚቃ መስራቱን ቀጥሏል፡፡ በዚሁ የሙዚቃ ቡድን ውስጥ ሙዚቃ ብቻ ሳይሆን ግብረ ገብን እና መልካም ስነ ምግባርን ማዳበሩንም ይናገራል፡፡ ‹‹ውትድርና ማለት አንድ ታላቅ ትምህርት ቤት ማለት ነው፡፡ ስርአት ወዳለው ሕይወት ራስህን የምትቀይርበት አንደኛው ቦታ ውትድርና ነው። ከሙዚቃው ጋር የውትድርናውን ሳይንስም አብሬ ተምሬያለሁ›› በማለት ይነገራል፡፡ ይህ የውትድርና ኪነት ግን ለአበበ የሙዚቃ ብቻ ሳይሆን የትዳሩም ጥንስስ የተጠነሰሰበት ነው፡፡ የዚሁ የኪነት ቡድን ተወዛዋዥ አባል የነበረችውን እና የሙያ ባልደረባው የነበረችውን ብሎም የዘፈነላትን እና ያለቀሰላትን እታገኝ ሙላትንም ያገኘው እዚሁ ነው። በኋላ ላይ ከእሷ ጋር መለያየቱንም በማስመልከትም ነው መከፋቱን እና የውስጡን መጎዳት በዜማ የገለጸው። ‹‹ሙዚቃ በፍቅር ውስጥ ሆነህ ስትሰራው እና እንዲሁ ስትሰራው በጣም ልዩነት አለው፡፡ ፍቅር ስልህ ደግሞ ከአብሮ መኖር በላይ በመለያየት ውስጥ ስትሆን ነው ፍቅርን የምታገኘው፡፡ ከባለቤቱ ጋር



ከተያየሁ በኋላ የማላውቃቸው የተደበቁ ጥበቦች ሁሉ ከኔ ላይ ወጡ ማለት ነው፡፡ በውስጥህ ያለው እንዲገለጽ የግዴታ መታመም አለብህ በሆነ ነገር›› ይላል፡፡

አርቲስት አበበ ተካ በ603ኛ ኮር ውስጥ የሙዚቃ መሰረቱን ቢጥልም የውትድርናው ሀላፊነት በኪነት ቡድን ውስጥ ያለውን ሀላፊነት እየገደበው ሲመጣ ከውትድርና ጠፍቶ አመለጠ፡፡ እናም ሙሉ ጊዜውን ለሙዚቃ ሰጥቶ በሚወደው ሙያ ለውጥን ያመጣው በምሽት ክበቦች ውስጥ በመስራቱ እንደነበር ያስታውሳል፡፡ አበበ አዲስ አበባ ውስጥ ኮንኮርድ እና ኦሪዮን በተሰኙ ምሽት ክበቦች ውስጥ በሰፊው ሰርቷል። ከላፎንቴኖች ጋር አብሮ የምሽት ክበብ ቢመሰርቱም ከአንድ ቀን በላይ አብሯቸው እንዳልሰራ ያስታውሳል።

በ1982 ዓ.ም የሰራው የመጀመሪያ አልበሙ በተለያዩ ምክንያቶች በህዝብ ዘንድ በሰፊው አለመደመጡን አበበ ያስታውሳል፡፡ ይሄው አልበም ከወጣ ከ4 ዓመታት በኋላ ነው በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያገኘው ‹‹ሰው ጥሩ›› የተሰኘውን አልበም ለህዝብ ጆሮ ያቀረበው፡፡ ‹‹የዚህ ስራ ውጤት የጓደኞቼ ታላቅ ጥረት ነው፡፡ በተለይ አበበ ብርሃኔ፤ ሙሉጌታ ተስፋዬ እና ጸጋዬ ደቦጭ ማለት ነው፡፡ የእነሱ ውጤት ነው፡፡ እንደኔ እንደኔ ልጅነት የሚያጠቃው ሰው፤ ጓደኛ የሚወድ ፤ ከሙያው በላይ አንዳንዴ ጓደኝነት የሚያጠቃው ሰው ነኝና በምክር እና በመደጋገፍ ነው እዚህ የደረስኩት›› ይላል ስለ አልበሙ ሲያወራ፡፡

አበበ ስራዎቹን በመድረክ ሲያቀርብ ራሱንና ውስጡን በማዳመጥ ጆሮውን ይዞ አይኑን ጨፍኖ በማዜም ይታወቃል፡፡ ይህ የተመስጦ ዘዬ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው አርቲስት አበበ ይናገራል። ‹‹አንድ ጆሮህን በምትይዝበት ጊዜ ጭንቅላትህ ላይ ነው ድምጽ ያለው፡፡ እና የራስህን ድምጽ ደግመህ ስለማትሰማው ያለመንሸራተት እድል አለህ፡፡ ልክ ከሳውንድ ሚክሰሩ ወጥቶ የምትሰማው ነው የሚመስለው፡፡ ሌላው አይኔን በምጭፍንበት ጊዜ አለማየትህ የሚሰበስበው ብዙ ነገር አለው››፡፡

አበበ ተካ ባህር ተሻግሮ አሜሪካ የገባው ከእሱ ቀድማ አሜሪካ የገባችውን ያዜመላትን ሚስቱን ለማግኘት ነበር፡፡ ያም ሆኖ አሜሪካ እሱ እንደጠበቀው አልጋ በአልጋ ሆና አልጠበቀችውም፡፡ ገና እሱ ዋሽንግተን ዲሲን እንደረገጠ ለእስር ተዳረገ፡፡ በእስር ቤት ቆይታው ደግሞ ሙዚቃን የሀሳቡ መገለጫ የብቸኝነቱ መግፊያ አድርጓት ቆይቷል፡፡ አርቲስት አበበ ተካ ከእስር ቤት ብዙ መማሩን ያስታውሳል፡፡ ‹‹እስር ቤት ማለት ከፍለህ የማትማርበት ትምህርት ቤት ማለት ነው፡፡ እና ወደዚህ አገር ስመጣ ያጋጠመኝ እስር ነበር፡፡ ምናልባት የመጀመሪያዋ ሌሊት ነበረች በሞት እና በሕይወት መካከል የነበርኩት። ምናልባት የዚያን ቀን ሞት መጥቶ ቢጠይቀኝ ወደ ሞት እሄድ ነበር። ነገር ግን ከአንድ ቀን በኋላ እስር ቤትን እንደ ቤቴ አየሁት። በወቅቱ አምስት ዓመት ነበር የተፈረደው ነገር ግን ባለኝ ስነ ምግባር በዓመት ከሁለት ወር ከእስር ቤት ተለቅቄያለሁ›› በማለት ወቅቱን ያስታውሳል፡፡

ከእስር ቤት እንደወጣም በሎስ አንጀለስ ከተማ በሚገኙ የምሽት ክበቦች ውስጥ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከዚያም ወደ ዋሽንግተን ሲቲ እና አካባቢዋ በማቅናት በዲሲ በሜሪላንድ እና በቨርጂኒያ የምሽት ክበቦች ውስጥ ሰርቷል፡፡ የሶስት ልጆች አባት የሆነው አበበ ተካን በተመለከተ የአድናቂዎቹ የሁልጊዜም ጥያቄ አዳዲስ ስራዎችን ይዘህ የምትመጣው መቼ ነው የሚል ነው፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት አሞኛል ብዬ የተሰኘ ነጠላ ዜማ ለቅቆ የነበረ ሲሆን በህዝብ ዘንድም በጣሙን ተወድዶለት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ የጤና እክል አጋጥሞት የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ጤናው ተስተካክሏል፡፡

# የፊደል መምህራችን - ቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ-ቡልጋ

በሰሜን ሸዋ ዞን የበረኸት ወረዳ ምክር ቤት ፅ/ቤት መስከረም 8/2015 ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ጉባኤ በወረዳው በመጠናቀቅ ላይ ያለውን የቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የፊደል አባት ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ኮሌጅ በሚል ስያሜ እንዲጠራ ወስኗል፡፡ እኛም ይህን አስደሳች ዜና ከሰማን በኋላ ስለ ታላቁ ሰው ልናስታውስ ወደድን፡፡

ከእፅዋት ቀለም አንጥረው፣ ከሸምበቆ ብዕር ቀርፀው፣ የፍየል ቆዳ ፍቀውና አለስልሰው በመጻፍ “ሀ..ሁ... ዕውቀት ይስፋ፣ ድንቁርና ይጥፋ – ይህ ነው የኢትዮጵያ ተስፋ” የሚል መፈክር ተጠቅመው ወደ ማህበረሰቡ ያዘለቁት “የፊደል ገበታው ጌታ” ቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሄረ-ቡልጋ የተወለዱት ሰሜን ሸዋ፣ ቡልጋ ከታብ ወይራ አክርሚት ከተባለ ቀበሌ ነው፡፡ ከአባታቸው ከመምህር ገብረሥላሴ ቢልልኝና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሥዕለሚካኤል ወልደአብ ታኅሳስ 24፣1895 ነው የተወለዱት፡፡

“የፊደል ገበታ አባት” የሚል ቅፅል መጠሪያ ያገኙት ተስፋ ገብረሥላሴን የሕይወትና የስራ ታሪክ የሚያስቃኘው መፅሃፍ፤ ስለአማርኛ የፊደል ገበታ ፈጣሪዎች ማንነትና ዘመን ማብራሪያ ባይኖረውም፣ ባለታሪኩ በመጀመሪያ በብራና ላይ በእጃቸው እየፃፉ፣ በመቀጠልም በማተሚያ ቤት ማሽን እያባዙ ለህዝብ እንዲደርስ አድርገዋል፡፡ “የአማርኛ የፊደል ቅርፅ በወቅቱ በእንጦጦ ማርያም፣ በባዓታ ለማርያምና በመካነየሱስ ስላሴ አጥቢያዎች እንዲሁም በገጠር አብያተ ክርስትያናት፤ በገዳማትና በዋሻዎች ብቻ ተወስኖ” እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ተስፋ ገብረስላሴ በ1909 ዓ.ም የ15 ዓመት ልጅ ሆነው ከትውልድ መንደራቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ያረፉበት መንደር አራት ኪሎ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን ከአራት ኪሎ የከተማዋ ደማቅ አካባቢ፤ አዝማሪ የማይታጣበት የቆንጆዎች መቀጣጠሪያ ነበር” ይላል በመፅሃፉ ገፅ 29 የሰፈረ መረጃ፡፡ ተስፋ ገብረሥላሴ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ሰርተው ራሳቸውን ለመቻል በእንጨት ፈለጣ፣ ውሃ በመቅዳት፣ ጉድጓድ በመቆፈር፣ በጎዳና ንግድ እና መሰል ትናንሽ ስራዎች ላይ ተሳትፈዋል፡፡


ነጋድራስ አቡበከር ከጅቡቲ ከሚያስ መጧቸው በተለይ ሽቶ እየተቀበሉ በየሆቴሉ ዞረው ሸጠዋል፡፡ በዘመኑ በአራት ኪሎ መንደር በንግድ ስራቸው በጣም ታዋቂ የነበሩት ነጋድራስ አቡበከር የአፋር ብሄረሰብ ተወላጅ ነበሩ፡፡ ከፈረንሳይ አገር የሚያስመጡትን ሽቀጥ በጅቡቲ በኩል ወደ አዲስ አበባ በማስገባት አገልግሎት ሲሰጡ በዕድሉ ከተጠቀሙት አንዱ ነበሩ፡፡

ክስ፣ እስርና ውንጀላ ያልተለያቸው ባለታሪክ የተስፋ ገብረሥላሴን የስራና የሕይወት ታሪክን ማዕከል አድርጎ የአገራችንን ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮች በስፋት የሚያስስ “ዘመን ተሻጋሪ ባለ-ውለታ” መፅሃፍ፤ ባለ ታሪኩ የህዝብና የአገር ባለውለታ መሆን የቻሉት በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፈው እንደሆነ ይገልፃል፡፡ በንጉሱ ዘመን (ከኢጣሊያ ወረራ በፊትና በኋላ)፣በጠላት ወረራ ወቅት፣ በደርግም አገዛዝ ለክስ፣ ለእስርና ውንጀላ ተዳርገዋል፡፡ በመጨረሻ ሁሉንም አሸንፈው በተደጋጋሚ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

ከአፄ ኃይለሥላሴ መንግስት የቀኝ አዝማች ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ደጋግሞ አመስግኗቸዋል፡፡ ታላቅ ተግባርና ትልቅ ስም አርቆ መድረሻን ለማቀድ፣ ከብዙ ጥረትና ልፋት የሚገኝ ነው። በዓመታት ድካም የተገነባ መልካም ተግባርና ስም ሊጠፋ፣ ሊረሳና ሊዘነጋ የሚችልባቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡

እኔ ከሞትኩ በኋላ ጥረትና ድካሜ ምን ይሆናል ብሎ ቀድሞ አለማሰብ ታላቅ ተግባርና ስም እንዲጠፋ ሰበብ ከሚሆኑት አንዱ ነው። በ1991 ዓ.ም ቤተሰቦቻቸውን ባለ አክሲዮን በማድረግ ኃ.የተ.የግ.አ/ማህበር ስራና መልካም ተግባራቸው እንዳይጠፋ ማድረግ ችለዋል፡፡ ተስፋ ገብረስላሴ ግንቦት 26 ቀን 1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ፣ የ97 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ነበሩ።

# ስፖርት





## ሉቺያኖ ቫሳሉን በጨረፍታ

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ ለጠነሰሰችው የአፍሪካ ዋንጫ ባይተዋር ብትሆንም ዛሬ ላይ የምትኮራበት አንድ ህያው ታሪክ አላት። ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የሆነውን ይህን አኩሪ ታሪክ ከጻፉ ጀግኖች መካከል የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው ደግሞ ሉቺያኖ ቫሳሎ ነው። ኢትዮጵያ 3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጅታ ስታስቀር የብሔራዊ ቡድኑ አምበል የነበረው ሉቺያኖ አገሩ ዳግም ለተመሳሳይ ክብር በቅታ ሳይመለከት ባለፈው ሳምንት በ87 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። የሉቺያኖ ቫሳሎ ስርዓተ ቀብር በጣልያኗ ሊዶ ከተማ ቅድስት ሞኒካ ቤተ - ክርስቲያን ተፈጽሟል። በዛሬው የስፖርት ማህደር አምዳችንም ይህ ታላቅ የእግር ኳስ ሰው ከብቸኛው የኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ ድል ጋር ከብዙ በጥቂቱ እናስታውሰው።

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ብቸኛውና ትልቁ ድል ሲገኝ የቡድኑ መሪ የነበረው ሉቺያኖ በ1927 በኤርትራ አስመራ ነው የተወለደው:: ሉቺያኖ የተወለደው ከጣሊያናዊ ወታደር አባቱ ቪቶሪዮ ቫሳሎና ከኤርትራዊት እናቱ መብራክ አብርሃም ነው:: ሉቺያኖ በኤርትራ ይኖሩ ከነበሩት በርካታ ቅይጥ ማንነት ካላቸው ዜጎችም አንዱ ነበር:: የዚህ ታላቅ ሰው ታሪክ አንድም በታላቅ ስኬትና ገድል የሚጠቀስ በሌላ በኩል ደግሞ በመገለል፣ ጭቆና እና ስደት የተከበበ መሆኑን እሱን በተመለከተ የተፃፉ ድርሳናት ያሳያሉ::

ከምንም ነገር በላይ ቀልድና ጨዋታ አዋቂነቱ የሚነገረው ሉቺያኖ እግር ኳስን መጫወት የጀመረው በአስመራ የተጎሳቆሉ መንደሮች ውስጥ ነው:: በአስመራ ከሚገኙ ኃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች አንዱ የነበረው ኮሌጂዮ ላቬላ የሉቺያኖ የእግር ኳስ ሕይወት መሰረት ነው:: ይህ የካቶሊክ ካቴድራል ትምህርት ቤት ስቴላ አስመሪና (የአስመራ ኮከብ) ተብሎ የሚጠራ የእግር ኳስ ቡድን ነበረው:: ጥቁርና ነጩ የቡድኑ መለያ በጣልያን-ኤርትራዊ (ኢታሎ-ኤርትራ) ጥንድ-ማንነት ላይ የተመሠረተው ቡድን መገለጫ እንደነበር ታሪኩ ያስረዳል።

ሉቺያኖ በስቴላ አስመሪና በግራ መስመር ተከላካይነት መጫወት ቢጀመርም ከቡድኑ ጋር ለረጅም ጊዜ ሳይቆይ የሌሎች ክለቦችን ትኩረት አገኘ:: የአገሪቱ የምድር ባቡር ሰራተኞች ሉቺያኖ ላይ አይናቸው አረፈ:: ‹ግሩፖ ስፖርቲቮ ፌሮቬሪ› በኤርትራ የባቡር ድርጅት ክለብ ሲሆን ሉቺያኖን በባቡር መንገድ ጥገና ሰራተኝነትና በተጫዋችነት ለመቅጠር ድርድር ቢያደርግም የተጫዋቹ ልብ ግን ወደ ሰማያዊ ለባሾቹ ገጀረት አደላ:: ማረፊያውም ይሄው ክለብ ሆነ::

ሉቺያኖ በገጀረት እ.ኤ.አ ከ1953 -1958 በነበረው የስድስት ዓመት ቆይታ ቡድኑን ወደ ከፍተኛው የሊግ እርከን እንዲያድግ አድርጓል:: በዚህ ወቅት ሉቺያኖ ያሳይ የነበረው ድንቅ ብቃትም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኞች አይን ውስጥ አስገባው። በእርግጥ ሉቺያኖ ከድሬዳዋ ጥጥ ማህበር እስከ ቅዱስ ጊዮርጊስ ድረስ በበርካታ ክለቦች ተነገረው የማያልቁ ብዙ ታሪኮች አሉት። እኛ ግን ለዛሬ ወደ ታላቅነት የተንደረደረበትንና በብሔራዊ ቡድን የነበረውን ቆይታ ብቻ እየተመለከትን እንቀጥል።

ሉቺያኖ ለግሩፖ ዲፖርቲቮ አስመራ ክለብ መጫወት ሲጀምር እድሜው ገና በ20ዎቹ አጋማሽ ላይ ነበር:: በተከላካይ መስመር ተጫዋችነት ጀምሮም ክህሎቱን በማሳደግ የጨዋታ አቀጣጣይ ለመሆንም ጊዜ አልፈጀበትም:: ጨዋታን የመምራት ብቃቱ እየጎለበተ የሄደው ሉቺያኖ በጠንካራ ምቶቹ ይታወቅም ጀመር::

እ.ኤ.አ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች ከኤርትራ የተገኙ ነበሩ:: ከነዚህ ተጫዋቾች አንዱ ሉቺያኖ ቫሳሎ ነው:: የመጀመሪያ የብሔራዊ ቡድን ጥሪ የደረሰውም እ.ኤ.አ በ1956 ነበር። 3ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በአራት ቡድኖች መካከል በኢትዮጵያ አዘጋጅነት ሲካሄድ ታሪካዊው ተጫዋች መንግስቱ ወርቁ ሉቺያኖ የቡድኑ አምበል እንዲሆን ትልቁን ሚና ተወጥቷል። የአፍሪካ ዋንጫው በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ስታዲየም ሲጀመር ሉቺያኖ የእግር ኳስ ታምራቱን ማሳየት የቻለው ገና በመጀመሪያው ግጥሚያ ነበር። የመጀመሪያ የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታ በሉቺያኖ 2 ግቦች፣ በመንግስቱ 1 ጎልና በተክሌ ኪዳኔ ተጨማሪ 1 ጎል አማካኝነት ኢትዮጵያ ቱኒዝያን 4-2 ረታች::

በፍፃሜው ጨዋታ ግብጾች ገና በ35ኛው ደቂቃ ኢትዮጵያ ላይ ባስቆጠሯት ግብ እስከ 75ኛው ደቂቃ ድረስ መምራት ቻሉ። 75ኛው ደቂቃ ላይ ግን ተክሌ ኪዳኔ ኢትዮጵያን አቻ አደረገ:: ግብጽም መልሳ መሪነቷን ለማግኘት ጊዜ አልፈጀባትም። ጨዋታው ሊጠናቀቅ 6 ደቂቃዎች ሲቀሩ ግን ሉቺያኖ ያስቆጠራት ግብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንን ወደ ዳግም አቻነት መለሰች:: ይህች ጎል የግብጾችን ሞራል አወረደች:: በጭማሪው ሰዓት ኢትዮጵያውያኖች በተዳከሙት ግብጾች ላይ ከፍተኛ ብልጫን ወሰዱ:: የሉቺያኖ ወንድም ኢታሎና መንግሥቱ አከታትለው ያስቆጠሯቸው ግቦችም ኢትዮጵያን 4ለ2 አሸናፊ አደረጓት። ኢትዮጵያም የመጀመሪያውንና ብቸኛውን የአፍሪካ ዋንጫ አሸነፈች:: በአስመራ ከጣሊያናዊ አባትና ከኤርትራዊት እናት የተወለደው ሉቺያኖም ከአፄ ኃይለሥላሴ እጅ ዋንጫ ተቀብሎ ወደ ላይ ከፍ አደረገ::

በኢትዮጵያ የንጉሳዊው ስርዓት ሲያበቃና ደርግ ስልጣን ሲይዝ ሉቺያኖ ኳስ መጫወት አቁሞ ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን በጣሊያን ታዋቂ በሆነው የእግር ኳስ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ማዕከል ኮቨርሲያኖ ከአርማንዶ ፒቺ ፣ ሴዛሬ ማልዲኒና ሉዊስ ቪንሲዮ ጋር በመማር በአሰልጣኝነት ብቅ አለ። ግን ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ብዙም ስኬታማ አልነበረም። በብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝነትም ብዙም ሳይዘልቅ 1976 ላይ ከአሰልጣኝነቱ ተነስቶ በጀርመናዊው ፒተር ሺንግተር ተተካ። ከጊዜያት በኋላም የብሔራዊ ቡድኑ ተጫዋቾች “አምፌታሚን ካፕታጎን” የተባለ አነቃቂ፣ ጉልበት ሰጪና የምግብ ፍላጎት የሚቀንስ መድሀኒት መጠቀማቸውን ማውገዙና መንቀፉ በአዲሱ መንግሥት በጠላትነት እንዲፈረጅ አደረገው:: በእርግጥ ብሔራዊ ቡድኑን በድጋሚ እንዲያሰለጥን ጥያቄ ቀርቦለት በ1978 በአሰልጣኝነት የመጨረሻ ጨዋታው ምስራቅ ጀርመንን ታሪካዊ በሆነ ሁኔታ አሸነፈ:: ከጨዋታው ሁለት ሳምንት በኋላም በጠዋት ወደ በጅቡቲ አድርጎ በካይሮ በኩል አሁን ሕይወቱ ወዳለፈባት ጣሊያን እንዳመራ ተጽፏል።



ሉቺያኖ ቫሳሉ ከአፄ ኃይለሥላሴ እጅ ዋንጫ ተቀብሉ ወደ ሳይ ከፍ ያደረገበት ታሪካዊ ፎቶግራፍ፣




## ቤተ መጽሐፍትን በፈረስና በአህያ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**


ልጆች እንዴት አላችሁ፤ አዲሱ የትምህርት ዓመት እንዴት እየሄደ ነው? እርግጠኛ ነኝ ጥሩ ነው ብላችሁኛል። ምክንያቱም ከናፈቃችኋቸው ጓደኞቻችሁና መምህራኖቻችሁ ጋር ተገናኝታችኋል:: በዚያ ላይ በጉጉት የጠበቃችሁት የትምህርት ጊዜ ተጀምሯል:: እናም ደስተኛ ጊዜን እያሳለፋችሁ እንደሆነ እገምታለሁ:: ዛሬ ደግሞ የበለጠ ደስተኛ የሚያደርጋችሁና ከትምህርታችሁ ጋር የሚገናኝ ነገር እነግራችኋለሁ:: ምንድነው ካላችሁ ንባብን ይመለከታል:: ሁሉም ሕጻን በእኩል ደረጃ የማንበብ እድሉ እንዲኖረው የሚያደርገውን አንድ ግብረ ሰናይ ድርጅት እነግራችኋለሁ::

ድርጅቱ «ኢትዮጵያ ሪድስ» ይሰኛል:: በልጆች ንባብ ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚሰራ ነው:: ይገርማችኋል ልጆች ይህ ድርጅት በጋራ መኖሪያ መንደር ውስጥ ሳይቀር ዘመናዊ የህፃናት ቤተ መጽሐፍት እየሰራ ልጆች አንባቢ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው:: በአዲስ አበባ ላሉ ልጆች የተለያዩ ቦታዎች ላይ ቤተ መጽሐፍትን የሰራ ሲሆን፤ አንዱ በቅርቡ በጋራ መኖሪያ ቤት አካባቢ የሰራው ጎተራ አካባቢ የሚገኘው ቤተ መጽሐፍት ነው:: ከዚያም ውጭ በሀዋሳም ይህንኑ ያደርጋል:: እናም በእነዚህ ሁለት ከተሞች የሕፃናትና የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት በመክፈት በአካባቢ ላሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች የንባብ አገልግሎት ይሰጣል::

ልጆች ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በሁሉም ክልሎች ከ70 በላይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቤተ መጻሕፍትን አቋቁሟል:: በዚህም እስካሁን ድረስ ከ130,000 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች፣ መምህራንና ሌሎች የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ በተለያዩ ትምህርትና ንባብ ተኮር በሆኑ ፕሮግራሞች ድጋፍ አድርጓል:: በተጨማሪም ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ከ300,000 በላይ የአገር ውስጥና የውጭ አገር መጻሕፍትን በተለያየ መንገድ ለሕፃናትና ለተማሪዎች አድርሷል::

ከመጽሐፍ ኅትመት ጋርም ተያይዞ ድርጅቱ ከዚህ በፊት ያሳተማቸው መጽሐፍ አሉት:: ሀገርኛ ሲሆኑ፤





ስድስት ቋንቋዎችን ያካተተም ነው:: በ22 ርዕሶች በማዘጋጀትና በማሳተም በአዲስ አበባ፣ በሐዋሳ፣ በሲዳማ በባህር ዳር፣ በጎንደር፣ በደሴ፣ በድሬዳዋና በሐረሪ ክልሎች ለሚገኙ 300 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለይም ከ1ኛ እስከ 4ኛ ላሉ ተማሪዎች በቤተ መጻሕፍት ውስጥ እንዲጠቀሙ አስችሏል::

ልጆች ኢትዮጵያ ሪድስ በክረምት መርሃ ግብር ሳይቀር የተለያዩ አስተማሪ፣ አዝናኝ እና የክህሎት ማጎልበቻ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የሚሰራ ነው:: ባሳለፍነው ክረምትም ለአምስት ሳምንታት ከቅደመ መደበኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ልጆች የክረምት ጊዜአቸውን በተሻለ ሁኔታ እውቀት እየገበዩ፣ መጽሐፍ እያነበቡ፣ ያላቸውን ልዩ ልዩ ችሎታ እያጎለበቱ እና በተለያዩ መዝናኛዎች እየተዝናኑ እንዲቆዩ አድርጓል::

ኢትዮጵያ ሪድስ ዓመታዊ የሕፃናት ንባብ ጉባዔም ያካሂዳል::እንደውም በቅርቡ ለሦስተኛ ጊዜ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ- መጽሐፍት አገልግሎት (ወመዘክር)ና ትም ህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን አካሂዷል:: የዚህ ዋና ጉባኤ አላማ የማንበብ ባህልን ማሳደግ፣ ሙያዊ ትምህርትን ለቤተ መጻሕፍት ዕድገት ማድረግ፣ አገራዊ መጽሐፎችን ውጤታማነታቸውና ፈተናዎ ቻቸው ማሳየትና የኢትዮጵያን የንባብ ባህል ማስተዋወቅ ነው::

ከዝግጅቶቹ መካከል የመጽሐፍ ንባብ፣ የተለያዩ ትምህርት አይነቶች ጥናት እገዛ፣ የቋንቋ ትምህርት (ቻይንኛ እና አረብኛን ጨምሮ)፣ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ትምህርት፣ የጥሩ ስብእና ግንባታ ትምህርት፣ ስፖርት፣ ሙዚቃ፣ ስነ-ስዕል፣ የተለያዩ መዝናኛ ጨዋታዎች (ገበጣ፣ ቼዝ) እና ሌሎች ይጠቀሳሉ::

ልጆች ኢትዮጵያ ሪድስ መቼ እንደተመሰረተ ታውቃላችሁ? እ.ኤ.አ. 2002 ነው:: ራዕዩም ሁሉም ሕፃናት በአካልና በሥነ ልቦና የማደግ ዕድል እንዲኖራቸውና በትምህርታቸውም ጠንካራና በራስ የመተማመን ስሜት ኖሯቸው እንዲያድጉ ነው:: ከዚህም ባሻገር የንባብ ባህልን፣ ትምህርትን በማስፋፋትና በማሳደግ ወላጆች ልጆቻቸውን በትምህርታቸው በመደገፍ ብርቱ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋል:: ለተማሪዎቹም ምቹና ደኅንነቱ የተጠበቀና የማንበብ ፍላጎትን የሚጨምር ሥፍራን በመፍጠር እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የልጆች መጻሕፍትን ማሳተምን ዋነኛ ዓላማው አድርጎ የሚሰራ ነው:: በኢትዮጵያ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ትምህርትና ቤተ መጻሕፍት ተኮር ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በክልሎች፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች በመሥራትም ላይ ይገኛል:: እዚህ ላይም ነው ፈረስና አህያን በመጠቀም ቤተ መጻሐፍት እንዲኖሩ ያደረጉበትን ነገር የምናነሳው::

ትምህርት ቤት ባልተከፈተባቸውና ራቅ ያሉ በአን ዳንድ የደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች በንባብ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል:: እንዴት ከተባለ ከላይ እንዳልኳችሁ መኪና አይገባምና ፈረስና አህያን ይጠቀማሉ:: ከአምስት ሺህ ለሚበልጡ ሕፃናትም በዚህ ሁኔታ ደርሰዋል:: ይህንን ሲያደርጉ በየመንደራቸው በመግባት መጻሕፍትን ይዞ የንባብ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ነው::

ልጆች ብዙዎቻችሁ የምታውቁት ቤተ መጽሐፍት በቤት ውስጥ ያለ ነው:: መደርደሪያዎቹ የሚያምሩ ናቸውም:: ከዚያ በመቀጠል የምታነቡባቸው ጥሩ ጠረጴዛና ወንበሮችም አሏቸው:: ቤተመጻሐፍት ባትሄዱም በቤታችሁ ቤተሰቦቻችሁ የሚገዙላችሁ አጋዥ መጽሐፍት ይኖሯችኋል:: እናም የማንበብ እድላችሁ በጣም ሰፊ ነው። በፈረስና በአህያ እየተጫኑ የሚሄዱበት የቤተመጽሐፍት አገልግሎት ግን ከዚህ በብዙ መልኩ የተለየ ነው::

የመጀመሪያው ባልተመቻቸ ቦታ ውስጥ ያሉ ልጆችን መደገፍ ሲሆን፤ ሩቅ ተሄዶ የማንበብ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩበት የሚደረግበት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ቦታው ባይመችም ልጆቹ እንዲያነቡ እድል የሚሰጥበት መሆኑ ነው:: እናም እንደ እናንተ ቤት አለያም ቤተመጽሐፍት የሚመች ቦታ ላይ ባይቀመጡም መጽሐፍ ግን አግኝተው ያነባሉ:: እንዴት ሆነው ካላችሁ ደግሞ በድንጋይ ላይ አለያም በዛፍ ስር ተቀምጠው ነው። በእርግጥ መጽሐፉ ሲጓጓዝ በሁለት አይነት መልኩ ነው። አንደኛው ሙሉ ለሙሉ በጀርባቸው ላይ አድርጎ በመጫን ሲሆን፤ ሁለተኛው እንደጋሪ ተደርጎ የሚጎተት ነው:: በውስጡ መቀመጫም ሊኖረው ይችላል። ይህ ማለት ተማሪዎች ሊያነቡ ሲሉ እንደእናንተ በወንበር ላይ የመቀመጥ እድል ሊያገኙ ይችላሉ:: ታዲያ ልጆች ኢትዮጵያ ሪድስን አታደንቁትም:: ይህንን እያደረገላችሁ ነው:: ስለዚህ እነዚህን ልጆች እያሰባችሁ በአቅራቢያችሁ ያሉ ቤተመጽሐፍትን ሳትጠቀሙባቸው እንዳታልፉ ላስጠነቅቃችሁ እወዳለሁ:: በሉ ለዛሬ በዚህ ልሰናበታችሁ:: በሚቀጥለው በሌላ ጉዳይ እንገናኛለን:: መልካም ሰንበት!!